# አዲስ ዘመን

እንድ

ማክሰኞ

82ኛ ዓመት ቁጥር 220 ሚያዝያ 10 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



pepsi


## “የሱዳን ሕዝብ ካጋጠመው ሁኔታ ለመውጣት የሚያስችለው ጥበብና ችሎታ ያለው ሕዝብ ነው”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- የሱዳን ሕዝብ አሁን ካጋጠመው ሁኔታ ለመውጣት የሚያስችለው ጥበብና ችሎታ ያለው ሕዝብ ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) አስታወቁ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የሱዳንን ወቅታዊ ጉዳይ በተመለከተ ባስተላለፉት መልዕክት ፤ የሱዳን ሕዝብ አሁን ካጋጠመው ሁኔታ ለመውጣት የሚያስችለው ጥበብና ችሎታ ያለው ሕዝብ ሲሉ ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በመልዕ ክታቸው፤ የጎረቤት አገር ሱዳን ሕዝቦች ከጥንትም ጀምረው ነፃነታቸውን የሚወዱ እና ብሔራዊ ክብራቸውን አስጠብቀው የቆዩ ሕዝቦች መሆናቸውን አስታውቀዋል።

የሱዳን ሕዝብ ከሚወሳባቸው አያሌ መልካም ባሕሪያት መሐከልም ለጋስነት እና እንግዳ ተቀባይነታቸው ከምንም በላይ ጎልቶ ይጠቀሳል ብለዋል።

የሱዳን ሕዝብ በባሕሪው ኩሩ በመሆኑ በምንም ሁኔታ ክብሩን እና ነፃነቱን አሳልፎ የሚሰጥ እንዳልሆነ የጠቀሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ የሱዳን ሕዝብ የራሱን ችግር በራሱ የመፍታት ታላቅ አቅም እና ጥበብ ያለው ታላቅ ሕዝብ በመሆኑ ጣልቃ ገብነት የሚያስተናግድ አይሆንም ሲሉ ገልጸዋል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ይህ ኩሩ የሱዳን ሕዝብ አሁን ላይ እየገጠመው ያለውን ቀውስ በጥበብ ሊወጣው ይችላል ስንል ያለንን ፅኑ እምነት ለመግለፅ እንወዳለን ሲሉ በመልዕክታቸው አስፍረዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳስታወቁት፤ የሱዳን ሕዝብ የራሱን ችግር በራሱ እንዲፈታ መተው ያለበት ሲሆን የማንኛውም የውጭ


“የሱዳን ሕዝብ ... ወደ ገጽ 2 ዞሯል


## ፊና ኦሮሚያ- የአርብቶ አደሩ እስትንፋስ

አስቴር ኤልያስ



“ከብቶች ነበሩኝ፤ ይሁንና በተከሰተው ድርቅ ምክንያት አለቁ። የነበሩኝ ከብቶች ለእኔም ለልጆቼም የመኖራችን መሠረት ነበሩ። ይሁንና ፈጣሪ የፈቀደውን ነው ያደረገው በሚል እጃችንን አጣጥፈን ተቀምጠን ባለንበት በአካባቢያችን ለውሃ ማቆር ነው ተብሎ ለግድብ ሥራ ሲቆፈር አስተዋልን። ከየት የሚመጣ ውሃ ይገባ ይሆን በሚልም ማስተዋል ጀመርን። ድንገት ግን ፈጣሪ ደግ ነውና መጋቢት ውስጥ በዘነበው ዝናብ ግድቡ ሞላ። የእኛም ተስፋ በዚያው ልክ መሙላት ጀመረ ይላሉ” የቦረና ዞን የአሬሮ ወረዳ የፉልዳዋ ቀበሌ ነዋሪው አርብቶ አደር ዲድ ገልማ።

ፕሮጀክቱ መቼም ትልቅ ስጦታችን ነው፤ እውነት ለመናገር ሲቆፈር እውነት አልመሰለኝም ነበር። በባዶ ሜዳ ይህ ሁሉ ድካም ስንልም ነበር። የፊና ኦሮሚያ ፕሮጀክት ግን የሚሠራውን ጠንቅቆ ያውቅ ስለነበር ድንገት ቀዬያችን የውሃ ባለቤት መሆን መቻሉን አስተዋልን ሲሉ ይናገራሉ።

ዛሬ ግመሎቻችንና ከብቶቻችን ከዚህ ግድብ ውሃ በመጠጣት ላይ ናቸው። ስለሆነም በጣም እናመሰግናለን፤ ይሆናል ያላልነውን ውሃ አሁን ግን በዓይናችን አየነው። መንግሥት ትልቅ ብር ወጪ አድርጎ በአዋቂዎች ግድቡ እንዲሠራ አድርጎልናል።


ፊና ኦሮሚያ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ፎቶ - ጸሀይ ንጉሴ

## “ለውጡን ለማሻገር ምሑራን፣ ማኅበረሰቡና ፖለቲከኞች ሂደቱን ሊደግፉት ይገባል”

- ዶክተር ዳባ ጩፋ የሕግ አማካሪ እና ጠበቃ

ዘላለም ግዛው

አዲስ አበባ ፡- በኢትዮጵያ እየተካሄደ ያለው ለውጥ እንዲሻገር ምሑራን፣ ማኅበረሰቡና ፖለቲከኞች በጎውን በጥሩነቱ በማድነቅ ሊሻሻል የሚገባውን ደግሞ ድርሻ በመውሰድ ሂደቱን በለውጥ አስተሳሰብ ሊደግፉት እንደሚገባ የሕግ አማካሪ እና ጠበቃ ዶክተር ዳባ ጩፋ ገለጹ።

ዶክተር ዳባ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ለውጡን ለማስቀጠል ምሑራን፣ ማኅበረሰቡና ፖለቲከኞች በጎውን በጥሩነቱ አድናቆት ሊሰጡት፣ መሻሻል የሚገባውን ደግሞ ከመተቸት አልፈው ድርሻቸውን በመውሰድ የበኩላቸውን ሊተገብሩ ይገባል።


“ለውጡን ለማሻገር ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል


## ኮንትሮባንድና ሕገወጥ ንግድን ለመከላከል ተቋማት ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ ኮሚሽኑ አሳሰበ

ዘላለም ግዛው

አዳማ፡- ኮንትሮባንድ እና ሕገወጥ ንግድን አደጋ መሆን ወደማይችልበት ምዕራፍ ለማድረስ የክልል እና የፌዴራል ተቋማት ኃላፊነታቸውን ባግባቡ እንዲወጡ እና ተገቢ የሕግ ርምጃ እንዲወስዱ የጉምሩክ ኮሚሽነር ደበሌ ቃበታ ገለጹ።

ኮሚሽነሩ ከሚዲያና ኮሙኒኬሽን አካላት ጋር የታክስ እና የጉምሩክ ሕግ ተገዢነት ሀገራዊ ንቅናቄ ዙሪያ


ኮንትሮባንድና ሕገወጥ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ዜና

# የአዲስ አበባ ወጣቶች ዛሬ በሃገራዊ ጉዳይ ይወያያሉ

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- በወጣቶች ግንባር ቀደምትነት የመጣው ለውጥ ያስገኘውን ቱሩፋትና ስኬት ለመዲናዋ ወጣት በማስረዳትና ለውጡን እንዲያስቀጥል የሚረዳ ውይይት እንደሚደረግ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ አስታወቀ።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ አቶ በላይ ደጀን በትናንትናው ዕለት በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ፤ በወጣቶች ግንባር ቀደምትነት በሀገሪቱና በመዲናዋ የመጣው ለውጥ ያስገኘውን ስኬት ለወጣቱ የማኅበረሰብ ክፍል በማስረዳት ለውጡን ለማስቀጠል በአስራ አንዱም ክፍለ ከተሞች ውይይት ይደረጋል።

ውይይቱም በመዲናዋ ከሚገኙ ወጣቶች ጋር የሚደረግ ሲሆን ሀገራዊ ለውጡ ለከተማዋ ያስገኘው ቱሩፋት፣ ወጣቶች ለሀገር ግንባታ ያላቸው ጉልህ ሚና፣ የወጣቶች ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን በዝርዝር የሚዳስስ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

የመጣው የለውጥ ቱሩፋትና ስኬት ወጣቱ እንዲገነዘብ ይደረጋል ያሉት አቶ በላይ፤ በተጨማሪም ለውጡ እየገጠመው ያለው ተግዳሮት ለውይይት እንደሚቀርብ ተናግረዋል። በዚህም ወጣቱ ተግዳሮቶችን በመፍታት የድርሻውን እየተወጣ ለውጡን ለማስቀጠል ያስችላል ተብሎ እንደሚጠበቅ አብራርተዋል።

የመዲናዋ ወጣቶች በውጭና የውስጥ ሀገር አፍራሽ ኃይሎችን የጥፋት አስተሳሰብ በማስቀረት ሀገር ግንባታ ላይ እንዲረባረቡ የሚያስችል ውይይትም ነው ሲሉ ጠቁመዋል ።

በመዲናዋ የሚታየውን የወጣቶችን የሥራ አጥነት ቁጥር ለመቀነስ ከተማ አስተዳደሩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራበት ነው ያሉት ኃላፊው፤ ወጣቱ የመዲናዋን ሀብት አሟጦ በመጠቀም ለፍቼ ደክሜ ያልፍልኛል የሚል አስተሳሰብ ለመፍጠር ውይይቱ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት ጠቁመዋል።

ውይይቱ የወጣቶችን በከተማዋ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ጤናማ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርጉና በሀሳብ የበላይነትና በምክንያት የሚያምኑ ዜጎች እንዲሆኑ የሚደረግ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ወጣቱ የሚያነሳቸውን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጥያቄዎች የከተማ አስተዳድሩ በየደረጃው ምላሽ እንዲሰጥ በማድረግ ወጣቱ ለጥፋት ኃይሎች ተገዢ እንዳይሆንና የመጣውን ለውጥ እንዲያስቀጥል ያለመ ውይይት ነው ሲሉ ጠቁመዋል።



ፎቶ - ጸሀይ ገጉሴ

አቶ በላይ ደጀን



# በሦስት ወራት 80 የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች ተጠግነው ወደ ሥራ ገብተዋል

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ባለፉት ሦስት ወራት በብልሽት ምክንያት ቆመው የነበሩ 80 የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች ተጠግነው ወደ ሥራ መግባታቸውን የአዲስ አበባ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት አስታወቀ። በቅርቡ ከ20 በላይ አውቶቡሶች ጥገና ተደርጎላቸው ወደ አገልግሎት እንደሚመለሱ ተገልጿል።

የአዲስ አበባ የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት ድርጅት ምክትል ዋና ሥራ አስኪያጅ ኢንጂነር አዳነ አብደታ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤በተለያዩ ምክንያቶች የተሽከርካሪዎች ብልሽትና አደጋ ያጋጥማል፤ ባለፉት ሦስት ወራት 80 አውቶቡሶች ጥገና ተደርጎላቸው ወደ ሥራ ተመልሰዋል። የአውቶቡስ ጥገናው በከተማው ውስጥ በሚገኙ አምስት ቅርንጫፍ ማዕከላት በመካሄድ ላይ መሆኑንም ገልጸዋል።

እንደ ኢንጂነር አዳነ ገለጻ፤ በከተማዋ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች አቅርቦት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ነው። አዲስ ከሚገቡ በተጨማሪ ብልሽት ለሚያጋጥማቸው አውቶቡሶች የመለዋወጫ ዕቃዎችንና የሰው ኃይልን በማሰባሰብ ጥገና በመደረግ ላይ ነው።

በከተማዋ 86 የተማሪና 950 በላይ የሕዝብ ማመላለሻ አውቶቡሶች አገልግሎት በመስጠት ላይ መሆናቸውን የገለጹት ምክትል ሥራ አስኪያጁ፤ መጪውን ክረምት ታሳቢ በማድረግ በተሽከርካሪዎች ላይ የጎማ፣ የባትሪና ሌሎች ጥገናዎች እየተደረጉ መሆኑን አስታውቀዋል።

የሸገርና አንበሳ ባስ ተቋማት በቂ የሆነ የጥገና ባለሙያና የሰው ኃይል መኖሩን ገልጸው በተለያዩ የከተማዋ አካባቢዎች የጥገና ሥራው ይካሄዳል። በዚህም በቃሊቲ ፣ሸጎሌ፣መካኒሳ፣ሰሚትና የካ ቅርንጫፎች በመካሄድ ላይ ነው ብለዋል።

በሕዝብ ማመላለሻ መስመሮች ላይ የአውቶቡስ አቅርቦት ችግር እንዳይከሰት አስፈላጊው ጥገና በመደረግ ላይ መሆኑን ጠቁመው፤ በቂ የሆነ የሰው ኃይል በመመደብና መጪውን ክረምት ታሳቢ ያደረገ ሥራ በመሥራት ላይ መሆኑን አስረድተዋል።

ኢንጂነር አዳነ እንዳስታወቁት፤ ግጭትና ብልሽት የሚያጋጥማቸውን አውቶቡሶች በፍጥነት ወደሥራ ለማስገባት የሚረዳ ቅንጅታዊ ሥራ አለ። በቀጣይም በብልሽት ምክንያት የቆሙና መለዋወጫ የሚፈልጉ ከ20 በላይ አውቶቡሶችን በመጠገን ወደ መስመር ለማስገባት እየተሠራ ይገኛል።

መጪውን ክረምት ምክንያት በማድረግ ለአሽከርካሪዎች የግንዛቤ መፍጠሪያ ሥራ በመሥራት ላይ መሆኑን የገለጹት ኢንጂነር አዳነ፤ በተለይም ለአሽከርካሪዎች፣ለስምሪት ባለሙያዎችና ለአገልግሎት ክፍያ ተቀባዮች ከአመራር አካዳሚ ጋር በመሆን የአቅም ማጎልበቻ ሥልጠና እየተሰጠ መሆኑን ጠቁመዋል።

መጪው ጊዜ ክረምት ከመሆኑ ጋር ተያይዞ በብልሽት ምክንያት ተሽከርካሪዎች እንዳይቆሙ ለማድረግ የቅድመ ዝግጅት ሥራ ይሠራል። በዚህም በመንገድ ላይ አውቶቡሶች ሕዝብን ይዘው እንዳይቆሙ ለማድረግ የሚያስችል የክትትል ሥራ ይከናወናል ብለዋል።

ኢንጂነር አዳነ እንዳስታወቁት፤በተለያዩ የሥራ አጋጣሚዎች ግጭት የሚያደርሱ አሽከርካሪዎች ተመዝግበውና ለተከታታይ 10 ቀናት ሥልጠና ወስደው ወደ አገልግሎት እንዲመለሱ ይደረጋል።

# ሚኒስቴሩ የቱሪዝም ሳተላይት ሥርዓት ሊዘረጋ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- ሀገሪቱ በቱሪዝም ዘርፍ ያለችበትን ደረጃ የሚያሳውቅ እና ከቱሪዝም ዘርፉ የሚገኘውን ገቢ የሚያሳይ የቱሪዝም ሳተላይት ሥርዓት ሊዘረጋ መሆኑን የቱሪዝም ሚኒስቴር አስታወቀ። ሚኒስቴሩ ዘርፉን ለማዘመን ከሃገር ውስጥና ከውጭ ሀገር ከመጡ ባሙያዎች ጋር የምክክር መድረክ አካሂዷል።

በቱሪዝም ሚኒስቴር የቱሪዝም ፕሮሞሽን መሪ ሥራ አስፈፃሚ አቶ ይስፋልኝ ሀብቴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ ሀገሪቱ በቱሪዝም ዘርፍ ያለችበትን ደረጃ የሚያሳውቅ እና ከቱሪዝም ዘርፉ የሚገኘውን ገቢ የሚያሳይ የቱሪዝም ሳተላይት ሥርዓት በቅርቡ ይዘረጋል። ይህንን ለማድረግም ከተለያዩ ባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ ነው።

ሥርዓቱ በቱሪዝም የሚገኘውን ገቢ ከተለያዩ ተቋማትና ኤጀንሲዎች የተሰበሰበ የተስተካከለ መረጃ ያቀርባል ያሉት አቶ ይስፋልኝ፣ የሚዘረጋው የቱሪዝም ሳተላይት ሥርዓት ሀገሪቱ በቱሪዝም ከሌሎች ሃገራት አንጻር ያለችበትን ደረጃ የሚያሳውቅ ዘመናዊ ሥርዓት መሆኑን ጠቅሰዋል። ሥርዓቱን ተግባራዊ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑንም ጠቁመዋል።

የቱሪዝም ሚኒስቴር፣ ከፕላንና ልማት ሚኒስቴር፣ ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ፣ ከገቢዎች ሚኒስቴር፣ ከግሉ ዘርፍ እና ከሌሎች ተቋማት የተውጣጡ ባለድርሻ አካላት ጋር እየተሠራ መሆኑን አብራርተዋል።

በኬንያ የቱሪዝም ጥናትና ምርምር ኢንስቲትዩት ዋና ሥራ አስፈፃሚ ዴቪድ ጊቶንጋ እንደተናገሩት፤ ለአፍሪካ ቱሪዝም ዋና ችግሩ የዘርፉን ትክክለኛ መረጃ ማመንጨት አለመቻሉ ነው። የባለድርሻ አካላት በጊዜ የአመራር ፈረቃ ላይ ተገቢውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ አለመሆናቸውም በተመሳሳይ በዘርፉ ያለ ችግር መሆኑን ጠቁመዋል።

የቱሪዝም ሳተላይት ሥርዓቱ በቱሪዝም ዘርፉ ላይ የሚስተዋሉ ችግሮችን ለመቅረፍና ዘርፉ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላያ ያለውን ድርሻ በመለካት ለፖሊሲ ቀረጻ ትልቅ ግብዓት ይሆናል ያሉት ሥራ አስፈፃሚው፤ በዚህም ኬንያ የኢትዮጵያን ቱሪዝም ዘርፍ ለመደገፍ እና ያላትን ልምድ ለማካፈል ሁሌም ዝግጁ ናት ብለዋል።

ኬንያ ሥርዓቱን ከመተግበሯ በፊት ከዓለም አቀፍ ቱሪስቶች የምታገኘው ገቢ በቅጡ የማይታወቅ በመሆኑ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም የማታገኝ እንደነበር ጠቅሰውም፤ አሁን ግን ዘርፉ ከጠቅላላ የሀገሪቱ ምርት ውስጥ የአሥራ ሁለት በመቶ ድርሻ እያበረከተ ነው ብለዋል።

የኡጋንዳ የቲኤስኤ ኮሚቴ ጂም አዮሬኪር በበኩላቸው፤ ፕሮጀክቱ ከኢጋድ ቱሪዝም ማስተር ፕላን ጋር የተጣጣመ ብሔራዊ የቱሪዝም ማስተር ፕላን መሆኑን ገልጸው፤ ሂደቱ የቱሪዝም መረጃዎችን ለማግኘት ፣ ሥራን ለመገምገም እና የዘርፉን ቀጥተኛ አስተዋፅዖ ለማሳየት የሚያስችል መሆኑን ጠቁመዋል።

ሥርዓቱ በተቻለ ፍጥነት ወደ ተግባር እንዲገባ ኤጀንሲዎች፣ ተቋማት እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል ያሉት ጂም አዮሬኪር፤ በኡጋንዳ የቱሪዝም ዘርፍ አሥር በመቶ የውጭ ምንዛሪ እንደሚያበረክት ሥርዓቱን ተግባራዊ በማድረግ ማወቅ ተችሏል ብለዋል።

የብሔራዊ ኢኮኖሚ ሒሳብና ስታቲስቲክስ ዳይሬክተር አቶ ፈለቀ ደምሲሶን በበኩላቸው፤ የሳተላይት ሥርዓቱ በግል እና በመንግስት ኢንቨስትመንቶች ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ ክፍተቶችን በመለየት የንግድ ሚዛንን ይለካል። ከዚህም ባለፈ ቱሪዝምንና የወጪ ንግድን ለማሳደግ ይረዳል ብለዋል።

# “የሱዳን ሕዝብ ካጋጠመው ...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ጣልቃ ገብነት ዓላማም ሰላምን እና ድርድርን በተመለከተ ብቻ ሊሆን ይገባል።

የኢትዮጵያ መንግሥት እና ሕዝብ በበኩሉ የሱዳን ሕዝብ የውስጥ ችግሩን በለመደው ጥበባዊ አካሄድ በራሱ እንዲፈታ የሚመኝ እና የሱዳን ሕዝብ ጥቅም ተከብሮ ማየት ትልቁ ፍላጎቱ መሆኑን በድጋሚ እንገልጻለን ሲሉም ጠቅላይ ሚኒስትሩ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በተያያዘ ዜና የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን ከሱዳን ተጠባባቂ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አሊ ኤል-ሳዲግ አሊ ጋር በስልክ ተወያይተዋል።

አቶ ደመቀ በማኅበራዊ ትስስር ገጻቸው እንዳሰፈሩት፤ በስልክ ውይይታቸው ወቅት ኢትዮጵያ በሱዳን እየተካሄደ ያለው ውጊያ እጅጉን እንዳሳሰባት ገልጸውላቸዋል። ኢትዮጵያ ከሱዳን ሕዝብ ጎን መሆኗን በመግለጽም፤ በውጊያው ምክንያት ሕይወታቸውን ላጡና ለተጎዱ ዜጎችም መጽናናትን ተመኝተዋል።

ቀናት በቀሩት የረመዳን የጾም ወር ወንድም የሱዳን ሕዝብ በሱዳናውያን መፍትሔ ወደ ቀደመው ሰላሙና መረጋጋቱ እንደሚመለስ ሙሉ እምነት እንዳላቸው አቶ ደመቀ መግለጻቸውን ነው ኢዜአ የዘገበው፡፡

# በክልሉ በመጪው ክረምት ከ11 ሚሊዮን በላይ ችግኞች ለመትከል ታቅዷል

**ማሕሌት ብዙነህ**



አዲስ አበባ ፡- በጋምቤላ ክልል በመጪው ክረምት 11 ነጥብ 7 ሚሊዮን ችግኞች ለመትከል እንደታቀደ የክልሉ እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ልማት መምሪያ ቢሮ አስታወቀ።

የጋምቤላ ክልል እርሻ እና ተፈጥሮ ሀብት ልማት ቢሮ ኃላፊ አቶ አጃ ኩቸላ ለኢትዮጵያ ፕሬስ እንደገለጹት፤ የ2015 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር በሚከናወንበት በክረምት ወራት ውስጥ 11 ነጥብ 7 ሚሊዮን ችግኞችን ለመትከል ታቅዶ የቅድመ-ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ ነው።

ከነዚህ የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ውስጥ በዋነኝነት ከ100 በላይ የችግኝ ጣቢያዎችን የማዘጋጀት፣ የመሬት ምንጣሮ ፣ የሰው ኃይል እና የግብዓት አቅርቦት ማዘጋጀት እንዲሁም በሚያዚያ ወር ላይ የችግኝ ማፍላት ተግባር እንደሚከናወን ተናግረዋል።

አቶ አጃ እንደገለጹት በ2014 ዓ.ም የአረንጓዴ አሻራ መርሐግብር 9 ነጥብ 5 ሚሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ 10 ሚሊዮን ችግኞች ተተክለዋል። ከተተከለው ውስጥም 87 በመቶ የጽድቀት መጠን አለው። በዚህም መሠረት ካለፈው ዓመት የተሻለ የጽድቀት መጠን ለማስገኘት በስፋት እየተሠራ ነው።

ከተተከሉት ችግኞች ውስጥ የጫካ ችግኞች እና ለምግብነት የሚውሉ ችግኞች የሚጠቀሱ ሲሆን በቀጣይ ለምግብነት እና ለኢኮኖሚ የሚጠቅሙ ችግኞች ላይ በትኩረት በመሥራት ምርት እንዲሰጡ በማድረግ ለክልሉ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፣ የገቢ ምንጭ እንዲሆን እንዲሁም ለም እና ፍሬያማ የሆነ አካባቢ ለመፍጠር እየተሠራ ነው ብለዋል።

እስካሁን ባለው ሁኔታ በአካባቢው በተተከሉት ችግኞች ላይ በበጋ ወራት ላይ ለመቆጣጠር የሚያስቸግር ከፍተኛ የእሳት ቃጠሎ መኖሩ፣ የአካባቢው ማኅበረሰብ ስለደን ያላቸው ግንዛቤ በቂ አለመሆን፣ ለአደን በሚወጡበት ጊዜ ችግኞችን የመቁረጥና የማቃጠል ፣ ልቅ የሆነ የእንስሳት ግጦሽ ፣ በቂ የውሀ መጠን አለመኖር እንደተግዳሮት ይጠቀሳል ብለዋል።

በየትኛውም አካባቢ የሚተከሉ ችግኞች በጥሩ ሁኔታ ከጸደቁ ለአፈር መሸርሸር እና ውሀ ጥበቃ ሥራዎች ፣ንጹሕ አየር ከማግኘት ፣የውሀ አማራጮች ከመፍጠር አንጻር ፣ ከዚህ በፊት እየተሸረሸሩ መሬቶች መልሶ ለማስተካከል እና ተዳፋት የሚባሉት ቦታዎችን የተስተካከሉ እንዲሆኑ የማድረግ እንዲሁም ምርትን ለማሳደግ እና የገቢ ምንጭነት በመሆን በኩል ብዙ አስተዋጽዖ አለው።

የአካባቢው አብዛኛው ክፍል ምድረ በዳ ወይም ብዙ በእጽዋት ያልተሸፈነ በመሆኑ ምክንያት በሰውም ሆነ በአካባቢው በሚገኙ እንስሳት ላይ ጉዳት የሚደርስበት ሁኔታ አለ ያሉት አቶ አጃ፣ ችግኝ መትከል እና መንከባከብ ያለውን ከፍተኛ አስተዋፅዖ በመረዳት በክልሉ ለሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች ችግኞችን መንከባከብ ዙሪያ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችና የአቅም ግንባታ ሥልጠና ለመስጠት በሰፊው በመሥራት ለተያዘው እቅድ የተሻለ አፈጻጸምና የጽድቀት መጠን ለማፍራት እንደሚሠራ ገልጸዋል።



አቶ አብዱልከሪም መንግሥቱ

# በክልሉ

## አራት ሚሊዮን የሚጠጉ አጎበሮች ሥጋት ባለባቸው አካባቢዎች ተሰራጭተዋል

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል አራት ሚሊዮን የሚጠጉ የወባ መከላከያ አጎበሮች ሥጋት ባለባቸው አካባቢዎች ቢሰራጩም አሁንም የአጎበርና የኬሚካል እጥረት እንዳለ የክልሉ ጤና ቢሮ አስታወቀ።

የአማራ ክልል ጤና ቢሮ ምክትል ኃላፊ አቶ አብዱልከሪም መንግሥቱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ከፍተኛ የወባ ትንኝ ሥርጭትና መራባት ባለባቸው 45 ወረዳዎች የወባ መከላከያ አጎበር ተሰራጭቷል።

ሥጋት ባለባቸው አካባቢዎች ከሦስት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊዮን በላይ የወባ መከላከያ አጎበር ማሰራጨት መቻሉን አስታውቀው፤ ሆኖም አሁንም የአጎበር እና ኬሚካል የወባ ርጭት እጥረት እንዳለ ተናግረዋል።

የጤና ኤክስቴንሽን ባለሙያዎች ከፍተኛ የወባ ሥርጭት ባለባቸው አካባቢዎች ቤት ለቤት በመሄድ የወባ ምርመራ በማድረግና አስፈላጊውን መድኃኒት በመስጠት የታመሙትን የማዳን እንዲሁም የሥርጭቱን መጠን የመቀነስ ሥራ እየተሠራ መሆኑን አቶ አብዱልከሪም አስረድተዋል።

የወባ ሥርጭቱ ካለፈው ተመሳሳይ ዓመት ጋር ሲነጻጸር ጭማሪ አሳይቷል ማሳየቱን አያይዘው ተናግረዋል።

አቶ አብዱልከሪም አክለውም የወባ ሥርጭት ለመከላከል የአልጋ አጎበርና የቤት ውስጥ የኬሚካል ርጭት የሚያስፈልጋቸው ቀበሌዎችና ወረዳዎችን የመለየት ሥራ በተደራጀ መንገድ ተካሂዷል ሲሉ ገልጸዋል።

በወባ በሽታ በከፍተኛ ደረጃ አምራቹ ኃይል እየተጠቃ ሲሆን ቁጥሩ ቀላል የማይባል ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ሕፃናት እንዲሁም ቅድሚያ ማግኘት የነበረባቸው ነፍሰ ጡርና ጡት የሚያጠቡ እናቶች ተጎጂ እየሆኑ መሆኑን ጠቅሰው፤ ሆኖም በወባ ምክንያት የሚሞት ሰው መጠን የሥርጭቱን ያህል እንዳልሆነ እና አነስተኛ መሆኑን ጠቁመዋል።

የወባ ሥርጭቱ በሰኔ ወር እንደሚጨምር የገለጹት አቶ አብዱልከሪም በዚህም ሥርጭቱን ለመግታት ለኅብረተሰቡ ግንዛቤ የመፍጠር ሥራ፣ ለሚመለከታቸው ሙያተኞች ሥልጠና የመስጠት እና የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ተናግረዋል።

ትልልቅ የእርሻ ማሳ ባለባቸው ምዕራብ ጎንደር፣ መተማ፣ ቋራ፣ ጃዊ፣ ወልቃይት እና ሑመራ አካባቢዎች ላይ ብዙ የቀን የሠራተኞች ስለሚገኙ የጤና ሚኒስቴር በየዓመቱ የባለሙያ ድጋፍ ሲያደርግ እንደነበርም ጠቁመዋል።

# በከተማዋ የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ከስምንት ሺህ በላይ የሥራ እድል ተፈጥሯል

**መሳኩ ኤሮሴ**

አዲስ አበባ፡- ባለፉት ሦስት ዓመታት በአዲስ አበባ ውስጥ በተገነቡት እና በመገንባት ላይ በሚገኙ ትላልቅ ፕሮጀክቶች ለስምንት ሺህ 380 ዜጎች የሥራ እድል መፈጠሩን የከተማዋ የትላልቅ ፕሮጀክቶች ግንባታ ጽሕፈት ቤት አስታወቀ።

የጽሕፈት ቤቱ የኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አዲስ አረጋይ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ በከተማዋ በተገነቡት እና በአሁኑ ወቅት በመገንባት ላይ ባሉት ትላልቅ ፕሮጀክቶች በ2013 ዓ.ም ለሁለት ሺህ 16 ዜጎች፣ በ2014 ደግሞ ለሁለት ሺህ 836 ሰዎች እንዲሁም በ2015 ከአራት ሺህ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች በድምሩ ከስምንት ሺህ ለሚበልጡ ዜጎች የተለያዩ የሥራ እድሎች ተፈጥሮላቸዋል››

የሥራ እድሎቹ በማሽኖች ኦፕሬተርነት፣ በግንበኝነት፣ በለሳኝነት፣ በቀለም ቀቢነት፣ በፌራዮ፣ በጥበቃ፣ በፈታሽነት ለተሠማሩ ዜጎች የተፈጠሩ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ፕሮጀክቶቹ የሥራ እድል ከመፍጠራቸው ባሻገር በፕሮጀክቱ ተሳታፊ የሆኑት በርካቶች ከቀን ሠራተኝነት ተነስተው የሙያ ባለቤት መሆናቸውንም አቶ አዲስ አስታውቀዋል። በርካታ የሚሆኑት የቀን ሠራተኞች ከአሠሪዎቻቸው እውቀት እየቀሰሙ መሆናቸውን ጠቁመው፤ የቀሰሙትን እውቀት ተጠቅመው ከቀን ሠራተኝነት ወደ አናጺነት፣ ፌራዮነት፣ ለሳኝነት ተሸጋግረው የተሻለ ገቢ ማግኘት የቻሉ ዜጎች መኖራቸውንም ጠቁመዋል።

በፕሮጀክቶቹ ውስጥ ከተፈጠረው ቀጥተኛ የሥራ ዕድል በተጨማሪ የፕሮጀክቶቹ ግንባታ በሚካሄድባቸው



አቶ አዲስ አረጋይ

አካባቢዎች ኢ-መደበኛ የሥራ እድሎች መፈጠራቸውንም የጠቆሙት አቶ አዲስ፤ በርካታ ዜጎች የፕሮጀክቶቹ ግንባታ በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የመኪና ማቆሚያ የፓርኪንግ አገልግሎቶችን በመስጠት፣ በተላላኪነት፣ በሊስትሮነት፣ የሻይ ቡናና ቁርስ አገልግሎት ሰጪዎች ተጠቃሚ እየሆኑ እንደሚገኙም ጠቁመዋል።

የቴክኖሎጂ ሽግግርን እውን ለማድረግ ተቀጥረው የሚሠሩት ዜጎች ቴክኖሎጂ እና ልምድ እንዲቀስሙ ከሚሠራው ሥራ ጎን ለጎን የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ፕሮጀክቶቹ የሚገነቡበት ቦታ ድረስ በመሄድ ፕሮጀክቶቹን እንዲጎበኙ እየተደረገ መሆኑንም ጠቅሰዋል።

# ኢትዮጵያ በውሃ ላይ የሚሠሩና የድርድር አቅምን የሚያሳድጉ የምርምር ተቋማት ያስፈልጓታል

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በውሃ ላይ የሚሠሩና የድርድር አቅምን ማሳደግ የሚያስችሉ የምርምር ተቋማት እንደሚያስፈልጓት ተገለጸ። በውሃ ሀብታችን ላይ ያለንን ንቃተ ሕሊና ለማሳደግ በሥርዓተ ትምህርት አካቶ ማስተማር እንደሚገባም ተጠቁሟል።

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የብሉናይል የውሃ ምርምር ተቋም ተመራማሪና የፖለቲካል ሳይንስ ዓለም አቀፍ ጥናት ክፍል መምህር አቶ አበበ ይርጋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ ያላትን የውሃ ሀብት ለመጠቀም በምታደርገው ጥረት እስካሁን የመጣችባቸው መንገዶች ብዙ ውጣውረዶች ያሉበት ነው። ይህንንም ቆም ብሎ በማሰብ በአሁኑ ጊዜ ፍትሐዊ የውሃ አጠቃቀምን ለዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ ማስረዳትና መደራደር የሚስችል አቅም መፍጠር ያስፈልጋል።

እንደ መምህሩ ገለጻ፤ በኢትዮጵያ የውሃ ሀብት ላይ ብዙ የተሳሳቱ ትርክቶች አሉ። ኢትዮጵያ ስላላት የውሃ ሀብት ላይ በትምህርት ሥርዓቱ ላይ ቀርጾ በደንብ ለትውልዱ ማስተማር ስላልተቻለ ያለን የውሃ ንቃተ ሕሊና ዝቅተኛ ነው። የውሃ ሀብታችን በሚገባ መጠቀም ለምን እንዳልቻልን፤ እነማን ጫና እንደሚያደርጉብን ለይቶ መሥራት አስፈላጊ ነው።

ኢትዮጵያ የውሃ ማማ ናት የሚለው ትክክለኛ ያልሆነ ትርክት ነው ያሉት አቶ አበበ፤ በአንጻሩ ኢትዮጵያ በውሃ ድህነት ውስጥ ያለች አገር ናት። ኢትዮጵያ ወደ ተፋሰሱ አገራት የሚፈሱ በርካታ ወንዞች ቢኖሯትም ኢትዮጵያውያን የሚጠቀሙትና የተፋሰሱ ሀገራት የሚጠቀሙት የውሃ መጠን እኩል አይደለም። ከፍተኛ ውሃ የሚጠቀሙት የታችኞቹ የተፋሰሱ አገራት ናቸው። እኛ ውሃን በአግባቡ ካልተጠቀምን ማደግና መበልጸግ አንችልም ብለዋል።

የኢትዮጵያ አብዛኛው የውሃ ሀብት ወደ ጎረቤት አገራት የሚሄድ መሆኑን የጠቆሙት አቶ አበበ፤ ‹‹ውሃችንን በአግባቡ ካልተጠቀምን የበይ ተመልካች መሆናችን አይቀርም››፤ በአግባቡ መጠቀም ባለመቻላችን ውሃ በተፋሰሱ አገራት አላስፈላጊ ብክነት እየደረሰበት ነው። ኢትዮጵያ ለመጠቀም በምታደረገው ጥረት ተንኮልና ጫና በማሳደር ስም የማጠልሸት ሥራ ይሠራሉ። በእንዲህ አይነት ሁኔታ መቀጠል አስፈላጊ ስላልሆነ የውሃን ግንዛቤ ለማሳደግ የውሃ ሀብት ተመራማሪዎችና ባለሙያዎችን፣ ተደራዳሪዎችን፣ የመንግሥት ከፍተኛ መሪዎችን አንድ ላይ በማምጣት በሚገባ መሞገት የሚያስችል አቅም መፍጠር እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ግብጽን ጨምሮ የታችኞቹ የተፋሰሱ ሀገራት በዓባይ ውሃ ላይ ብቻ የሚሠሩ ብዙ የምርምር ተቋማት አሏቸው። ኢትዮጵያ እንደ አገር በውሃ ላይ የሚሠራ ራሱን የቻለ የምርምር ተቋም የላትም ያሉት ተመራማሪው፤ በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ የብሉ ናይል የውሃ ምርምር ተቋምና በአርባ ምንጭ ዩኒቨርሲቲም ደረጃ ውሃ ላይ የሚሠራ ምርምር ተቋም መኖሩን ጠቅሰዋል።

ነገር ግን እንደ ሀገር ጠንካራ የሆነ በውሃ ላይ ብቻ የሚሠራ የምርምር ተቋም መገንባት ያስፈልጋል ያሉት ተመራማሪው፤ ለመንግሥት ፖሊሲ ግብዓት የሚሆኑ ምርምሮችንና መረጃዎችን የሚያዘጋጁ አቅማቸው የጎለበት የምርምር ተቋማትን ማቋቋም አስፈላጊ መሆኑን አብራርተዋል።

የኢትዮጵያ አብዛኛዎቹ ወንዞች ወደ ጎረቤት አገራት የሚፈሱ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ በእያንዳንዱ ወንዝ ላይ ልማት ባካሄድን ቁጥር ከተፋሰሱ አገራት ጋር ያለን ግንኙነት በመልካም ጎኑ አይነሳም። ይህንን መመከት የሚያስችል መንግሥትን የሚደግፍ፣ሕዝብን የሚያነቃ፣ዲፕሎማሲን ውጤታማ ማድረግ የሚያስችል፤የድርድር አቅምን የሚያጎለብት የውሃ የምርምር ተቋማት ኢትዮጵያ እንደሚያስፈልጋት አቶ አበበ ገልጸዋል።



የጉምሩክ ኮሚሽነር ደበሌ ቃበቶ

## ኮንትሮባንድና ሕገወጥ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

በተካሄደው የምክክር መድረክ ላይ ኮሚሽነር ደበሌ እንደገለጹት፤ ተቋማት የተሰጣቸውን ኃላፊነት ባግባቡ አለመወጣት፤ በአሠራር፣ በአደረጃጀት እና የግብይት ዋጋን በትክክል ተደራሽ በማድረግ በተሟላ መልኩ ባለመሠራቱ ለኮንትሮባንድ ሂደቱ አስተዋፅዖ አድርጓል።

የሕግ ተገዢነትን ለማረጋገጥ የሚወሰዱ ርምጃዎችም ተከታታይነት ያለመኖር፣በሚያዙ ኮንትሮባንዲስቶች ላይ ተገቢ የወንጀል ምርመራ፣ የክስ አመሠራረት እና በፍርድ አሰጣጥ ላይ ጉድለቶች መኖር ከሚስተዋሉ ክፍተቶች መካከል እንደሚጠቀሱ አንስተዋል።

ኮንትሮባንድ እና ሕገወጥ ንግድ አደጋ መሆን ወደማይችልበት ምዕራፍ ለማድረስ ተቋማት የተሰጣቸውን ኃላፊነት ባግባቡ ሊወጡ ይገባልም ብለዋል ኮሚሽነር ደበሌ።

የኮንትሮባንድ ድርጊት አፈጻጸምና ባሕሪ ከጊዜ ወደ ጊዜ ውስብስብ እና ፈተና ሆኖ መቀጠሉንም ጠቁመዋል።

ሁኔታው የኮንትሮባንድ ሰዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ በብዙ ዘዴና ስልት ወንጀሉንና የወንጀሉን ድርጊት እንዲቀጥሉ ዕድል እንደሰጣቸው በመጠቆምም በተለይ ከጫት ፣ ከማዕድን ውጤቶች፣ ከግብርና ምርቶች፣ ከግንባታ ቁሳቁሶች፣ ከቁም እንስሳት ግብይት ጋር ተያይዞ ከገቢ እና ወጪ ንግድ ጋር ያሉትን ሁኔታዎች ማየት ይቻላል ሲሉም አስረድተዋል።

በክልል እና በፌዴራል የሚገኙ ተቋማት ተገቢውን ኃላፊነታቸውን በተናበበ መልክ እና በተከታታይ አለመወጣት ኮንትሮባንድ እና ሕገወጥ ንግድን በወሳኝ መልኩ አደጋ መሆን ወደማይችልበት ምዕራፍ ማድረስ አልተቻለም ሲሉም ነው የገለጹት።

በተቀናጀ መንገድ የክልል እና የፌዴራል ተቋማት ኃላፊነታቸውን በተቀናጀ መልኩ መወጣት እንዲሁም ተገቢ እና አስተማሪ የህግ ርምጃ መውሰድ እንደሚገባም አሳስበዋል።

ኮንትሮባንድ እና ሕገወጥ ንግድ በሀገር ላይ ከሚያደርሰው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ ችግር አንጻር አደጋውን ለመከላከል ባለፉት አራትና አምስት ዓመታት መሠረታዊ ሥራዎች መሠራታቸውን፣ በተለይ የፌዴራል ጉምሩክ፣ የፌዴራል ፖሊስና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ከክልሎች ጋር በመቀናጀት በተሠሩ ሥራዎች አደጋ ለመከላከል መቻሉን እና ከፍተኛ ውጤት መገኘቱንም ነው የጠቆሙት።

የገቢዎች ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ መሠረት መስቀሌ፣ ሚዲያ እና ኮሙኒኬሽን የጋራ መግባቢያ ለመፍጠር ሁነኛ መሣሪያ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

ከኅብረተሰቡ እና ከግብር ከፋዩ ጋር የጋራ ተግባቦት ለመፍጠር እንዲሁም በዘርፉ ውጤታማ ተግባር ለማከናወንም ጉልህ ሚና እንዳላቸውም ነው የጠቆሙት።

የሀገርን ኢኮኖሚያዊ እና ማኅበራዊ መሠረተ ልማትን ለማስፋፋት፣ ለልማት እቅድ ስኬትና ለሰላም መስፈን ኢኮኖሚው የሚያመነጨውን ገቢ በብቃት፣ በፍትሐዊነት እና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መልኩ መሰብሰብ አስፈላጊ መሆኑን ተናግረዋል።

ዘመናዊና የተሻሻለ የታክስ ሥርዓት መዘርጋት በዘርፉ የሚፈጸሙ ወንጀሎችን ለመከላከል ቁልፍ ተግባር እንደሆነም ነው የተናገሩት። የገቢዎች ሚኒስትርና ጉምሩክ ኮሚሽን የግብር አሰባሰብን ለማዘመን በትብብር ላይ የተመሠረተ ጤናማ የታክስ ሥርዓት ለመዘርጋት ሲሠሩ መቆየታቸውንና ትግበራው ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም ገልጸዋል።

ግልጽነት፣ ተጠያቂነት እና ውጤታማነትን ማረጋገጥ፣ ለኅብረተሰቡም ስለታክስ እና የጉምሩክ ሕጎች ግንዛቤ መፍጠር ይገባል ብለዋል።

በንግድ ሥርዓቱ ደረሰኝ የማይጠቀሙ፣ ታክስ የሚሰውሩ፣ በታክስ ማጭበርበር ሥራ ላይ የተሠማሩ፣ ግብር አሳንሰው የሚከፍሉ እንዲሁም በመሰል የዘርፉ የወንጀል ተግባር ላይ የተሰማሩትን ተጠያቂነትን በማስፈን እና በማስተማር ወደ ሕጋዊ መስመር ለማስገባት ትብብር ማድረግ እንደሚገባም ነው ያመለከቱት።

# “ለውጡን ለማሻገር ምሑራን፣ ማኅበረሰቡና...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

መንግሥት ደግሞ ሆደ ሰፊ እና ታጋሽ ሊሆን ይገባል ያሉት ዶክተር ዳባ፤ የተነሳበትን የለውጥ አመለካከት መሠረት ባደረገ መልኩ መሥራት እንደሚጠበቅበትም አመልክተዋል።

ለውጡን ለማስቀጠል መንግሥት ብቻውን ሊተገብር የሚችለው አድርጎ ማሰብ ተገቢ አይደለም። የፖለቲካ ምሑራን እና አመራሮች የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል ሲሉ ነው የጠቆሙት።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ለውጡ ተሻግሮ በኢትዮጵያ ጥሩ እንዲሆን በለውጥ እሳቤ ማሰብ ያስፈልጋል። ጥሩውን ማሞገስ እና ማበረታታት ያስፈልጋል። እንዲሁም ለውጡ የሚፈልገውን የራስን ድርሻ ወስዶ ለትግበራው መትጋት ይገባል።

ኢትዮጵያ ባለፉት ዓመታት በዓይነቱ የተለያየ ችግርን ያዘለ የፖለቲካ አስተሳሰቦችና አመለካከቶችን አስተናግዳለች። በተለይ ከአምስት ዓመታት ወዲህ መንግሥት በአገሪቱ ከታዩ የፖለቲካ አስተሳሰቦች ለየት ባለ መልኩ ኅብረተሰቡን ያሳተፈ የለውጥ መነሳሳት በመላበስ በቁርጠኝነት ሲንቀሳቀስ ቆይቷልም ብለዋል።

መንግሥት በቁርጠኝነት ለመለወጥ ኃላፊነት የወሰደው ባለፈው የፖለቲካ ዐውድ ውስጥ የነበረው ችግር ባልጠራበት ሁኔታ ነው። የቀደመው ባልተቀየረበት እንዲሁም ቀደም ሲል የነበረው አስተሳሰብ በቀጠለበት ሂደት ውስጥ ኃላፊነቱን በመውሰድ ለውጥ አመጣለሁ በማለት ሲንቀሳቀስ መቆየቱንም ነው የተናገሩት።

በሂደቱ በአንድ በኩል ባለፉት የፖለቲካ ምሕዳር ውስጥ የነበሩ ለውጡን ለመቀበል የማይፈልጉ ኃይሎች በመግፋት ፈተና ነበር፤ መንግሥት ለውጡን ለማሳለጥ አዲስ አስተሳሰብ ይዞ መነሳቱ ደግሞ በሌላ ወገን መንግሥትንም ሕዝብንም ዋጋ ሲያስከፍል ቆይቷል ብለዋል።

ያም ሆነ ይህ የሚታዩ ጭላንጭል ለውጦች አሉ። ለውጡ ተሻግሮ እውን እንዲሆን በመንግሥትም ሆነ በሕዝብ በኩል የሚቀሩ ተግባራትን ለይቶ ርብርብ ማድረግ ያስፈልጋል። ለውጥን ማሳለጥ የሚቻለው ጥሩውን ነገር በመደገፍ፣ መጥፎውን ደግሞ በማረም ሊሆን ሲገባ በማኅበረሰቡ የተለመደው እና እየሆነ ያለው የተለየ ነው ብለዋል።

ለውጡን ወደፊት ለማራመድ የሚደረጉ በርካታ ጥረቶች ቢኖሩም ወደ ኋላ የሚጎትቱ በርካታ አስተሳሰቦችና ድርጊቶች አሉ ያሉት ዶክተር ዳባ፣ ይህ ደግሞ ለውጡ በሚፈለገው መልኩ እንዳይሻገር እንቅፋት ፈጥሯል ብለዋል።

በመሆኑም ይህንን ችግር ለመሻገር ሁሉም ዜጋ፤ በተለይ ምሑራን እና ፖለቲከኞች ግንባር ቀደም በመሆን ለውጡ ለመላው ኅብረተሰብ ተጨባጭ እድገት ይዞ እንዲመጣ የበኩላቸውን ሊወጡ እንደሚገባ አሳስበዋል።

# ፊና ኦሮሚያ- የአርብቶ አደሩ ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ፈጣሪያችንንም መንግሥታችንንም እናመሰግናለን ይላሉ።

“ድርቁ ከፉ ነው፤ እኔ ቢያንስ ወደ 68 ያህል ከብቶች ነበሩኝ። ነገር ግን ባጋጠመን ድርቅ ምክንያት እንደዋዛ ከእጄ አጥቻቸዋለሁ” የሚሉት ደግሞ በዚሁ በቦረና ዞን፣ በሚኦ ወረዳ በባሃ ቀበሌ ነዋሪ የሆኑት አርብቶ አደር ዲዳ ሃቃ ናቸው። እንደ ቀበሌያችንም ሆነ እንደወረዳችን ከብት ያለው በጣም ጥቂት ነው ሲሉም ያክላሉ። አሁን ግን በቀበሌያቸው እየተገነባ ያለው ግድብ የማይታመን እንደሆነባቸው ነው የቆጠሩት። ሁሉም እንደሚያወቀው የቦረና ዞን የውሃ እጥረት አለበት። ዛሬ ግን ከውሃ እጥረት የተነሳ ምንም ማድረግ እንደማንችል አስሮ ያስቀመጠን ነገር ተፈቷል ማለት እችላለሁ ሲሉም ይገልጻሉ።

በተለይ የመጠጥ ውሃ ችግር የከፋ ነበር የሚሉት አርብቶ አደሩ፣ ይህ ለእኛም ሆነ ለምናረባቸው ከብቶቻችን ትልቅ ፈተና ሆኖ ቆይቷል። አሁን ግን ይላሉ አርብቶ አደሩ፣ ይህ እየተገነባ ያለው ግድብ ውሃ ከመያዙ የተነሳ በርከት ያለ ችግራቸውን እንደቀረፈላቸው ያመለክታሉ።

እርሳቸው እንደሚሉት፤ ግድቡ በአካባቢያቸው ተገንብቶ ውሃ በመያዙ ብቻ ከረሃብ እንደሚወጡ እርግጠኞች ሆነዋል። ለዚህ ደግሞ ምክንያታቸው እነርሱ እንደሌላው የሀገሪቱ ክፍል በመስኖ የተለያዩ የልማት ሥራዎችን መሥራት ያስችላቸዋል።

ድርቁ 230 ከብቶችን እንዳሳጣቸው የሚናገሩት የአሬሮ ወረዳ ፉልዳዋ ቀበሌ ነዋሪው አርብቶ አደር ኑራ ቢዱ በበኩላቸው፤ በቁጥር ጥቂት ይሁኑ እንጂ የተረፉ ከብቶች አሉኝ ይላሉ። “ድርቅ ጠራርጎ ባይገድልብኝ ኖሮ በርካታ ከብቶች ነበሩኝ፤ ዛሬ በእጄ የሚገኙት አምስት ከብቶች ናቸው፤ አሁን የተገኘው ውሃ እነዚህን ለማባዛት ያስችለኛል ብለዋል።

የድርቁ ጊዜ ጋብ ብሎ ዛሬ በአካባቢያችን በተገነባልን ግድብ ውሃ በመያዙ የእኛም የከብቶቻችንም አፍ ረጠበልን ይላሉ። በአሁኑ ወቅት ውሃው በአቅራቢያው በመሆኑ መስኖም በመማር ላይ እንዳሉ ይናገራሉ። ዝም ብለው ነው የሚቆፍሩት ስንል የነበረው ግድብ ውሃ ይዞልናል። እንደ እኛ ሐሳብ ውሃ የሚመጣ አልመሰለንም ነበር፤ ነገር ግን በተደረገው ሥራ መንግሥትን ከልክ በላይ አመስግነናል ሲሉ ይገልጻሉ። አርብቶ አደሩ፣ በቀጣይ ደግሞ መስኖ ልማት ላይ እንሳተፋለን ሲሉም ነው የተናገሩት።

የቦረና ዞን፣ የሚኦ ወረዳ አስተዳዳሪ አቶ አስቻለው ዮሐንስ እንደሚሉት ከሆነ፤ ወረዳው የአርብቶ አደር ወረዳ ነው። በመሆኑም በድርቅ ምክንያት የተለያየ ጉዳት ደርሶበታል። ነዋሪው አርብቶ አደር እንደመሆኑ መጠን የኑሮ መሠረቱ የሆኑት እንስሳት ናቸው። ይሁንና አካባቢው ባጋጠመው ድርቅ ምክንያት የወረዳው 90 በመቶ ያህሉ እንስሳት በሕይወት መትረፍ አልቻሉም።

አቶ አስቻለው፣ በቅርቡ በዘነበው ዝናብ መሠረት አካባቢው በአጭር ጊዜ ሊያገግም የቻለ ቢሆንም ቀደም ብሎ የደረሰው ጉዳት ከፍ ያለ እንደሆነ ይናገራል። ይሁንና ይህንን ችግር ከመሠረቱ ለመቀየር መንግሥት በክልሉ ፊና ኦሮሚያ በሚል ፕሮጀክት እቅድ አውጥቶ መንቀሳቀስ መጀመሩና ውጤቱም መታየት መቻሉ ለወረዳው ነዋሪ ትልቅ እፎይታን ሰጥቷል ይላሉ።

በተለይ እንደሚኦ ወረዳ የተሠራው ግድብ ቀደም ሲል በአርብቶ አደርነት ብቻ ይተዳደር የነበረው ነዋሪ የአኗኗር ስልቱን ቀይሶ ወደአርሶ አደርነትም እንደሚያዘነብል ይናገራሉ። ከዚህም የተነሳ ከብትን ተከትሎ ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀስ የነበረው አርብቶአደር በአሁኑ ወቅት አርሶም መብላት እንዲችል የተገደበው ውሃ ምቹ ሁኔታን የፈጠረ እንደሆነ ጠቅሰው፤ ለአርብቶ አደሩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ተሰጥቶት ወደዛው ሥራ እንደሚገባ ነው ያብራሩት።

የፊና ኦሮሚያ ፕሮጀክቶችን ግንባታ በምክትል ደረጃ በመምራት ላይ ያሉ የኦሮሚያ ክልል መስኖና አርብቶ አደር ምክትል ቢሮ ኃላፊ ኢንጂነር ዓለሙ ረጋሳ በበኩላቸው፤ በፊና ኦሮሚያ እየተገነቡ ያሉ ፕሮጀክቶች ሲያጋጠመን ለነበረው ድርቅ እንደ ሁነኛ መፍትሔ የሚቆጠር ነው ይላሉ። የፕሮጀክቱ ዓላማም በዋናነት ውሃ መያዝ ሲሆን፣ በመቀጠል ደግሞ ከሌሎች ሴክተር መሥሪያ ቤቶች ጋር በመሆን የመስኖ ሥራ እና እንደ ዓሣ ምርትና ሌሎች ተግባራት የሚከናወኑበት እንደሆነ ያስረዳሉ።

እርሳቸው እንደሚናገሩት፤ እንደ ኦሮሚያ ክልል ከተጀመሩ 73 ፕሮጀክቶች መካከል 14ቱ በቦረና የሚገኙ ሲሆን እነርሱም በሰኔ ሙሉ ለሙሉ ይጠናቀቃሉ። በዚህ በተያዘ ውሃ አርብቶ አደሩ ለመጠጥ ውሃነት እንዲሁም ለመስኖ ልማት ሊጠቀምበት ይችላል። ትልቁ ሀብት ለሆነው እንሰሳው ደግሞ መኖ ሊያለማበት ይችላል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አንድነቱ የጸና የአገር መከላከያ ለታላቋ ኢትዮጵያ!

አገር እንደ አገር የሉዓላዊነቷ ከፍታ የሚገለጠው፤ ሕዝብም እንደ ሕዝብ ያለ ልዩነት የደህንነት ስጋቱ ተወግዶ የተረጋጋ ሰላምን የሚያጣጥመው የሁሉም ሆኖ ለሁሉም በመቆም ዋጋ በሚከፍል የአገር መከላከያ ኃይል ነው፡፡ ምክንያቱም በአንድ አገር ውስጥ ጠንካራ፣ አስተማማኝ እና ከሁሉም ለሁሉም የሆነ የመከላከያ ኃይል እና የደህንነት ተቋም መኖር፤ ለአገርም ሁለንተናዊ ክብርና ከፍታ ዋልታ፤ ለሕዝብም የሰላምና ደህንነት አለኝታነቱ ለጥያቄ የሚቀርብ አይሆንምና ነው፡፡

በዚህ ረገድ አንቱታን ያተረፉ አገራት አሉ፡፡ ያኔ ዓለም እንዲህ በቴክኖሎጂና በተራቀቁ የኃይል ሚዛን ማስጠበቂያ የጦር ቴክኖሎጂዎች ባለቤት ባልሆነችበት ዘመን፤ ኢትዮጵያ በቴክኖሎጂው ከኋላ ሆና በጦር ኃይሏ ግን ከፊት ቀድማ ደማቅ ገድልን የጻፈች አገር ናት፡፡ የጥንቱ ቀርቶ የመካከለኛውና የቅርቦቹ አገራዊ ዓለም አቀፍ ገድሎቿ፤ እንዲሁም የውስጥ ሰላምና አንድነትን ያስጠበቁ ተግባሮቿ የጠንካራ ማዕከላዊ ኃይል ባለቤትነቷ ሕያው ምስክር ናቸው፡፡

ዛሬም ኢትዮጵያ በተለያዩ ችግሮችና ፈተናዎች እየተፈተነች ያለች ቢሆንም፤ እነዚህን ችግሮቿን በመሻገር ሂደት ውስጥ የመከላከያ እና ደህንነት ተቋማቷ ተኪ የሌለው ሚናቸውን በመጫወት ላይ ይገኛሉ፡፡ በዚህ ሂደት ግን ለእነዚህ ተቋማት አጋዥ የሆኑ ኢ-መደበኛ አደረጃጀቶች የመኖራቸውን ያህል፤ እነዚህ አደረጃጀቶች ደግሞ በሂደት አቅም እየፈጠሩና እየጠነከሩ በሄዱ ቁጥር ለአገር ሳይሆን ለክልል፤ ለሕዝብ ሳይሆን ለቡድን መጠቀሚያ በመሆን አገርንና ሕዝብን የሕልውና አደጋ ውስጥ ሲጨምሩ ታይቷል፡፡

ከዚህ መለስ ባሉ የሕዝብ ሰላምን በማደፍረስ፤ የዜጎችን የመዘዋወር፣ ሰርቶ ሃብት የማፍራትና በሕይወት የመኖር መብትን ጭምር አደጋ ላይ ሲጥሉም ተስተውሏል፡፡ እነዚህ አደጋዎች ለአገር ሉዓላዊነት አደጋ፤ ለዜጎችም ሰላምና ደህንነት ስጋት ከሆኑ ውለው አድረዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህ ለአገርም ሆነ ለዜጎች ፈተና የሆኑ ችግሮችን ከማስቀረት አኳያ እንደ መንግስት ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራበት ሲሆን፤ በተለይ በእነዚህ አደረጃጀቶች ምክንያት በአገር እና ሕዝብ ላይ ከተደቀነው አደጋ መቀልበስ እና ሰላምን መመለስ በተቻለ ማግስት፤ የክልል ልዩ ኃይል አደረጃጀቶች ያላቸውን አቅምና ልምድ ለጥፋት ሳይሆን ለላቀ አገራዊ አቅም እንዲያውሉ በሚያስችል መልኩ መልሶ የማደራጀት ተግባር ውስጥ ተገብቷል፡፡

ከእነዚህ መካከል አንዱ ልዩ ኃይሎች ከፍ ላለ አገራዊ ኃላፊነት እድል ያገኙበትን የአገር መከላከያ ሰራዊት አባል የመሆን ሂደት ሲሆን፤ የፌዴራል ፖሊስ እንዲሁም የክልል መደበኛ ፖሊስን ተቀላቅሎ ለላቀ ኃላፊነት መሰማራትንም ይጨምራል፡፡ ይሄንን አልሻም ያሉም በሲቪል መደበኛ ሕይወት ውስጥ ገብተው የሚኖሩበት እድል ተመቻችቷል፡፡ እነዚህ ልዩ ኃይሎች በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ እንዲቀላቀሉ የተሰጠው እድል ደግሞ አገር እንደ አገር ከፍ ያለ አቅም ያለው አንድነቱ የጸና የመከላከያ እና የደህንነት ኃይል ለመፍጠር እድል የሚሰጥ ሲሆን፤ ይሄንን እድል ለመጠቀም የወሰኑ የክልል ልዩ ኃይሎችም ተግባራቸው ሊመሰገንና ሊበረታታ የሚገባው ነው፡፡

ምክንያቱም የክልል ልዩ ኃይልነት ከአንድ አካባቢና ክልል የዘለለ አገራዊ ሕልምና ኃላፊነትን የሚነጥቅ ነው፡፡ በአንጻሩ የአገር መከላከያ ሰራዊት አባል መሆን ከአገር አልፎ ዓለማቀፍ ኃላፊነትን የመሸከም የገዘፈ ታላቅ ጥሪ ነው፡፡ ይሄ መጠራት ደግሞ ከሁሉም ለሁሉም የሆነ ኃይልን የመገንባት፤ የአገርን ሉኣላዊነትና ግዛት የማስከበር፣ ሕዝብንም የሰላምና ደህንነት ስሜት እንዲጎናጸፍ የማስቻል፤ ዓለምአቀፍ ተልዕኮንም ለመቀበል መጠራት ነው፡፡ በዚህ ረገድ ጥሪውን ተቀብሎና የመንግስትን ዓላማ ተረድቶ አዎንታዊ ምላሽ የሰጠው የልዩ ኃይል ብቻ ሳይሆን፤ መላው ሕዝብና ሌላውም ባለድርሻ የመልሶ ማደራጀቱን ዓላማ እና ግብ ተረድቶ መሰል አዎንታዊ ድጋፉን ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ ምክንያቱም ለአገር ክብርና ሉዓላዊነት፤ ለሕዝብም አብሮነት፣ ሰላምና ደህንነት የተበታተነ ኢ-መደበኛ አደረጃጀት ሳይሆን ጠንካራ እና አገራዊ የጸጥታ ኃይል እውን ማድረግ የግድ ስለሆነ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ትልቅ ሚና ያለው ደግሞ የመከላከያ ሰራዊት እንደመሆኑ፤ የአገር እና ሕዝብ የደህንነት ምንጭ የሆነውን መከላከያ ኃይል በማጠናከር ሁሉም የድርሻውን ሊወጣ ይገባል!


አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን
**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4240
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## መልኩን የቀየረው የህጻናት ጉልበት ብዝበዛ

**ስምስም መንግሥቱ**

የጎዳናውን ዳር ይዘው ወደላይና ወደታች የሚወርደውን መንገደኛ ‹ተመዘን ›እያሉ የሚማፀኑ ህፃናትና ታዳጊዎችን ማየት የተለመደ ነው:: ምንም አይነት መጠለያ በሌለበት ነው ቀኑን ሙሉ አላፊ አግዳሚውን ‹‹ተመዘን›› ሲሉ ይውላሉ:: አንዳንዶቹም የያዙት የክብደት መለኪያ ሚዛን ከእነርሱ አቅም በላይ ነው:: ምግብ ሲበሉም ሆነ ውሃ ሲሰጡ አያጋጥሙም:: ሆቴል ሄደው ይበላሉ ብሎ ለመገመት የገንዘብ አቅም ብቻ ሳይሆን እድሜያቸውም አይፈቅድም::

በአስቸጋሪ ሁኔታ በጎዳና ሥራ ላይ የተሰማሩት ህፃናትና ታዳጊዎች በእድሜ የበሰሉ ሰዎች እንኳን የሚቋቋሙት የሥራ አይነት አይደለም:: እነዚህ ህፃናትና ታዳጊዎች የወላጅ ወይንም የአሳዳጊ እንክብካቤ በሚያስፈልጋቸው፣ በትምህርት ገበታ ላይ በሚገኙበት እድሜያቸው ነው ከአቅማቸው በላይ የሆነ ጫና የተሸከሙት:: በእድሜያቸው የመጫወት እድል እንኳን ተነፍጓቸዋል::

በአይነህሊናዎ በወላጆቻቸው ወይንም ባሳዳጊዎቻቸው እንክብካቤ የሚደረግላቸውንና እነዚህ እጅግ ከአቅማቸው በላይ በሆነ ሥራ ውስጥ የሚገኙትን ልጆች ሲያዩ የእነዚህ ህፃናት እጣ ፈንታ ለምን እንዲህ ሆነ ብለው ማሰብዎ አይቀርም:: በእርግጥ የኑሮ ወይንም የኢኮኖሚ ሁኔታ የፈጠረው ልዩነት እንደሆነ ለሁላችንም ግልጽ ነው:: ግን ደግሞ ወላጅ ወይንም አሳዳጊ ልጆቹን ለከፋ ነገር አጋልጦ ይሰጣል ወይ? የሚለው ነው በትልቁ መሠመር ያለበት:: በአነስተኛ የሥራ መስክ ላይ ተሰማርተው ልጆቻቸውን በአቅማቸው የሚንከባከቡ ብዙ ወላጆችን በየአካባቢያችን እናስተውላለን::

እነዚህ የክብደት መለኪያ ሚዛን ይዘው በጎዳና ላይ ‹‹ተመዘን›› እያሉ የሚውሉ ህፃናት ጉዳይ ግን ይለያል:: ቋንቋቸው ተመሳሳይ ነው:: ይህ ደግሞ ከአንድ አካባቢ የመጡ ለመሆናቸው አንዱ መለያ ወይም ማሳያ ነው:: አብዛኞቹም በተመሳሳይ እድሜ ላይ የሚገኙም ናቸው:: ይሄ ሁኔታና የህፃናቱም አኗኗር ለምን? የሚል ጥያቄ ይፈጥራል:: በአንድ ወቅት በአዲስ አበባ ከተማ በተለምዶ ሽሮሜዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በስፋት የባህላዊ ሽመና ሥራ የሚሰሩ ግለሰቦች ከደቡብ የኢትዮጵያ ክፍል ህፃናትን በስርቆትና ወላጆቻቸውን በገንዘብ በማማለል ከጉያቸው እንዲወጡ በማድረግ ከእድሜያቸው በላይ በሆነው የሽመና ሥራ ላይ በማሰማራት ያደርሱ የነበረው የጉልበት ብዝበዛ በስፋት ይነሳ እንደበር ይታወሳል:: እነዚህ ልጆች ማምለጥ የሚችሉበት እድል እንኳን እንዳይኖር ከቤት አያስወጧቸውም:: ትምህርትቤትም መሄድ አይችሉም:: ቀኑን ሙሉ በጉድጓድ ውስጥ የሽመና ሥራ ሲሰሩ እንደሚውሉና የመኝታ ሰዓት እንደሚገላግላቸው ነበር ሲነገር የነበረው::

ህፃናቱ በአካልም በአእምሮም ነበር የሚጎዱት:: በአንድ ወቅት መገናኛ ብዙሃንን ጨምሮ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች አጀንዳ ሆኖ ጉዳዩ በስፋት ሲነሳ ነበር:: የነበረው ርብርብ ችግሩን ሙሉ ለሙሉ ባይቀርፈውም በህብረተሰቡ ዘንድ ግንዛቤ መፍጠሩ አይዘነጋም:: አሁን ደግሞ በህፃናት ላይ የሚደረገው የጉልበት ብዝበዛ መልኩን ቀይሮ መጥቷል:: በምንዘዋወርበት ጎዳና ልብሳችንን እየጎተቱና ከፊታችን እየቀደሙ እጃቸውን ለምጽዋት የሚዘረጉ የህፃናት ጉዳይም አንዱ ነው::

በተለይ ‹‹ተመዘን›› እያሉ በጎዳና ላይ ስለሚሰሩ ህፃናት ጉዳይ አንድ ወዳጄ እንዳጫወተኝ በአሰሪዎቻቸው ከፍተኛ የማስፈራራት ጫና ስለሚደረግባቸው አብዛኞቹ ስለሚደርስባቸው ችግር፣ የሥራ ጫና እና ስለቤተሰባቸው ሁኔታ ለመናገር አይደፍሩም:: የቀጣይ ኑሮአቸው ስለሚያሳስባቸው ዝምታን ይመርጣሉ:: ይህ ወዳጄ ባደረገው ከፍተኛ የማባበል ሙከራ የተወሰኑ ህፃናትን አነጋግሮ ወላጆቻቸው በማያውቁበት ሁኔታ ወደ አዲስ አበባ ከተማ እንዳመጧቸውና ያመጧቸውን እንደማያውቋቸው ነበር የነገሩት:: ህፃናቱ የቀን ገቢ ማስገባት ዋና ተግባራቸው ነው:: አሰሪያቸው በህብረት እንዲኖሩ ላመቻቸላቸው የኪራይ ቤት ደግሞ በጋራ በማዋጣት መክፈል ይጠበቅባቸዋል:: ምግባቸውንም የሚችሉት እራሳቸው ናቸው:: ይሄን ሁሉ ኃላፊነት ለመወጣት በየቀኑ መሥራት ይኖርባቸዋል:: የሥራ ስምሪታቸውም ከጠዋት 12 ሰአት እስከ ማታ 12 ሰአት ነው:: በዓለም አቀፍ ህግ አንድ ሰው በህግ አግባብ ለስራ እድሜው ከደረሰ በኋላ እንኳን በቀን ስምንት ሰዓት ብቻ እንዲሰራ ተቀምጧል:: በዚህ ላይም የዓመት ፈቃድ አለው:: ህጻናቱ ግን ባልመረጡት የእለት ኑሮቸው በዚህ ሁኔታ እንዲያልፍ ተገደዋል:: እነዚህ ህፃናት ላይ እንዲህ የፈረደው ሰው ግን በእነርሱ ጫንቃ ይኖራል::

ወዳጄ ያገኛቸው ህፃናት ወላጆቻቸው ናፍቀዋቸው እንደነበር ነው የነገሩት:: መረጃውን ስለሰጡት የሚደርስባቸውን ጫናም በመገንዘቡ ልጆቹን ከወላጆቻቸው ጋር ለማገናኘት መስዋእትነት ከፍሏል:: በወቅቱ የአንደኛው ህፃን እናት ልጃቸው ሞቷል ብለው ተስፋ ቆርጠው እንደነበርም ነው ልጃቸውን ይዞላቸው በሄደ ጊዜ ያጫወቱት::

ልጆቹን ወደወላጆቻቸው ለመቀላቀል ለወዳጄ ቀላል አልነበረም:: ለጊዜው ማቆያና ምግብ ከመቻል ጀምሮ ወላጆቻቸው ያሉበት ድረስ ለማድረስ ወጪና ጊዜን ይጠይቅ ነበር:: እንዲህ ባለው ሁኔታ አንድ ሰው የሚያደርገው ጥረት ልጆቹን ካሉበት ችግር ለመታደግ እጅግ ከባድ ሆኖ ነው ያገኘው:: እንደርሱ መስዋእትነት ለመክፈል ባልችልም ለግንዛቤ ብዬ አንዳንዶችን ለማነጋገር ሞክሬ ነበር:: ወዳጄ እንዳለው ልጆቹ ፍርሀት አለባቸው:: በቋንቋም ልንግባባ አልቻልንም::

‹‹ጋን በጠጠር ይደገፋል›› እንዲሉ ለእነዚህ ህፃናት ለመድረስ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንም የጋራ ትብብር ይጠይቃል:: በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ ህፃናት ላይ በተለያየ መንገድ እየተፈፀመባቸው ያለው የጉልበት ብዝበዛ ትልቅ አጀንዳ መሆን እንዳለበት ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በተካፈልኩበት ሥልጠና ላይ በነበሩ ተሳታፊዎች ተነስቶ የነበረው የተለያየ ተሞክሮ የጉዳዩን አሳሳቢነት ነበር የተገነዘብኩት::

በወቅቱ ስልጠናውን የሰጡን በኬር ኢትዮጵያ የፕሮጀክት ዳይሬክተር ወይዘሮ ፀደይ አማረ እንደነገሩን በህፃናት ላይ የሚፈፀም የጉልበት ብዝበዛን በተመለከተ የተደረጉ ጥናቶች የቆዩ ናቸው:: በተለይ በአገር አቀፍ ደረጃ የተደረገ ጥናት እኤአ በ2015 አካባቢ እንደሆነ ነው መረጃዎች የሚያሳዩት:: አሁን አገሪቱ በውስጥ በገጠማት የተለያየ ችግር ህፃናት ለጉልበት ብዝበዛ የበለጠ ተጋላጭ የሚሆኑበት እድል ስለሚሰፋ ቁጥሩን በትክክል ማስቀመጥ ይከብዳል ነው ያሉት እንደሚከብድም ተናግረዋል::

ኢትዮጵያ የህፃናት ጥበቃ (ቻይልድ ፕሮቴክሽን) ፖሊሲ ውስጥ የተካተተ ካልሆነ በስተቀር እራሱን የቻለ የህፃናት ጉልበት ብዝበዛ (ቻይልድ ሌበር) ፖሊሲ እንደሌላትም ገልጸዋል:: ይህም ህፃናት ላይ ከሚደርሰው የጉልበት ብዛበዛ አንፃር የተሰጠው ትኩረት አናሳ መሆኑን ያሳያል ነው ያሉት:: በአሁኑ ጊዜ የፖሊሲ ማሻሻያ እንዲደረግ ባለድርሻ አካላትን በስልጠና ግንዛቤ በማስጨበጥ እንዲሁም ህፃናት ላይ የሚደርሰውን ጉልበት ብዝበዛ አገራዊ ገጽታ የሚያሳይ የጥናት ሥራም ለመሥራት ኬር ኢትዮጵያ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል ብለዋል::

ኬር ኢትዮጵያ ከህፃናት ጉልበት ብዝበዛ ጋር በተያያዘ ከሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር ሥራዎችን እየሰራ ይገኛል:: በተጨማሪ ለተለያዩ ባለድርሻ አካላት የግንዛቤና ስልጠናዎችን በመሥጠት ንቅናቄ እንዲፈጠርም እንዲሁ እየሰራ ነው:: ባጠቃላይም በህፃናት ላይ የሚደርሰውን ጉልበት ብዝበዛ ለመከላከል ትምህርት ሚኒስቴር፣ ማዕድን ሚኒስቴርና ሌሎችም አስፈጻሚ አካላት ኃላፊነት እንዳለባቸውና እነዚህን ባለድርሻ አካላት ያካተተ ሥራም እንደሚያስፈልግ በመርሃግብሩ ተብራርቷል:: እኔም ይህንን የህጻናትን ህይወት የሚያጨልም የአገር ገጽታን የሚያበላሽ ተግባር እንዲገታ የሚመለከታቸው አካላት ትኩረት እንዲሰጡ ስል መልእክቴን አስተላልፋለሁ።

# ነፃ ሀሳብ



በቁምላቸው አበበ ይማም (ሞሼ ዳያን)
fenote1971@gmail.com

ቁምላቸው አበበ በአማራ ባህል፣ ቱሪዝምና ማስታወቂያ ቢሮ፤ በኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፤ በደቡብ መገናኛ ብዙኀን፤ በጋዜጠኝነትና በታሪክ ባለሙያነት ያገለገሉ ሲሆን፤ የደቡብ ኤፍ ኤምን ከባልደረቦቻቸው ጋር በመሆንም አቋቁመዋል።በፌዴራል ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅትና በአለ በጅምላ በኮሙዩኒኬሽን ዳይሬክተርነት አገልግለዋል። ከአአዩ በቋንቋና ታሪክ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን የሰሩ ሲሆን፤ በዚሁ ዩኒቨርሲቲ በጋዜጠኝነትና ኮሙዩኒኬሽን ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በማጠናቀቅ ላይ እያሉ ባጋጠማቸው ድንገተኛ ህመም ተስተጓጉሏል። ጥልቅ ሀሳብ ያዘሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ፁሑፎችን በማህበራዊ ሚዲያና በተለያዩ ጋዜጦች በማውጣት ይታወቃሉ።

## ምክክር በኑሮ ውድነት ላይ፤

ጸሐፊው በዚህ አምድ ስለዋጋ ግሽበቱና እሱን ተከትሎ እየተባባሰ ስለመጣው የኑሮ ውድነት ላለፉት ሁለትና ሦስት አመታት በተደጋጋሚ መጣጥፎችን በማጠናቀር ለማስነበብ ሞክሯል። የግልም ሆኑ የመንግሥት የህትመት፣ የኤሌክትሮኒክስና የማህበራዊ ሚዲያዎች እንዲሁ በዋጋ ግሽበቱና በኑሮ ውድነቱ ላይ እልፍ አእላፍ ዘገባዎችንና ፕሮግራሞችን ሠርተዋል። ሆኖ የተገኘው ውጤት እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። ጸሐፊው የሚፈለገውን ያህል ውጤት ሊገኝ ያልቻለው ባለድርሻ አካላት ተናበውና ተቀናጅተው ባለመሥራታቸው ነው ብሎ ያምናል። እንዲሁም ባለድርሻ አካላት የኑሮ ውድነቱን አሳሳቢነት በእኩል ደረጃ ተገንዝበውታል ብሎ አያምንም።

ስለሆነም በተለይ ሰው ሰራሽ የሆነውን የዋጋ ግሽበትና እሱን ተከትሎ እየተባባሰ የመጣውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋትና ዘላቂ መፍትሔ ለማግኘት ተቀናጅቶ መሥራት ስለሚያስፈልግና ከጊዜ ወደ ጊዜ ከኢኮኖሚያዊ ጉዳይነት ተሻግሮ ማህበራዊ ችግር እየኀነቀለ ፤ በዚህ የሚቀጥል ከሆነም የሰላም፣ የደህንነትና የጸጥታ ችግር ወደ መሆን እየዳኸ መገኘቱ ላይ ወጥ የሆነ ግንዛቤ ተጨብጦ የመፍትሔ ፍኖተ ካርታ ማስቀመጥ እንዲቻል እና አልበርት አነስታይን እንዳለው ችግሩን በፈጠረው አግባብ መልሶ መፍትሔ ማስቀመጥ ስለማይቻል ጸሐፊው ከተለመደው እይታ ወጣ ያለ አተያይ ይዞ መጥቷል። ችግሩን ከማራገብ ይልቅ መፍትሔ ለማመላከት ይሞክራል። ለዚህ ነው የዛሬው ጽሑፉ ችግሩ ላይ ሳይሆን ወደ መፍትሔነት ሊያመራ የሚችል የመነሻ ሀሳብ ማቅረብ ላይ ያተኮረው።

የዚህ መነሻ ሀሳብ አበይት አላማዎች ሁለት ናቸው። የመጀመሪያው ሰው ሰራሹን የኑሮ ውድነት ወይም ፈር የለቀቀውን የግብይት ሥርዓት ለማስተካከል የሚደረግ ጥረት በአንድ ወገን ወይም በመንግሥት ብቻ ዳር ሊደርስ ስለማይችል መላ ሕዝቡን ወይም ሸማቹን ማሳተፍ ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ አገር አቀፍ ንቅናቄን ማቀጣጠል ይጠይቃል። አገራዊ ምክክሩ ደግሞ በእርሾነት ማገልገል ግንባር ቀደም አላማው ነው።

የመነሻ ሀሳቡ ሁለተኛ አላማ ሻጩም፣ ሸማቹም፣ መንግሥትም፣ ባለድርሻ አካላት ማለትም የሃይማኖት ተቋማት ምክር ቤት፣ የአዲስ አበባ የንግድና የዘርፍ ማህበራት፣ ብዙኃን መገናኛዎች፣ እንደ የኢትዮጵያ ሸማቾች መብት ተቆርቋሪ ድርጅት ያሉ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ ወዘተረፈ የኑሮ ውድነቱ መፍትሔ ካልተበጀለት የህልውናና የደህንነት ስጋት ሊሆን እንደሚችል መግባባት ላይ በመድረስ በዚህ ልክ ኃላፊነታቸውን እንዲወጡ የጋራ ፍኖተ ካርታና የድርጊት መርሀ ግብር ማዘጋጀት ነው።

ኢትዮጵያ በአፍሪካ ከናይጄሪያ ቀጥሎ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያላት አገር መሆኗ ይታወቃል። አንዳንድ ይፋዊ ያልሆኑ መረጃዎች የሕዝብ ቁጥሯን እስከ 117 ሚሊዮን ይተነብያሉ። ይህ ሕዝብ፤ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ ሸማች ወይንም ሻጭ ነው። ዜጎች በአንድ አጋጣሚ ሸማች ሆነው በሌላ ጊዜ ደግሞ ሻጭ ይሆናሉ። ይህ ሁላችንም ሸማቾች እንደሆነ ያሳያል። የአገራችን ሸማች በተመጣጣኝ ዋጋ፣ ጥራት ያለው፣ ጤንነቱ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ ሸቀጥ አገልግሎት አማርጦ፣ አወዳድሮ የመሸመት መብት ቢኖረውም እውን ማድረግ ባለመቻሉ ለዘርፈ ብዙ ችግሮች ተዳርጎ ይገኛል።

ለኑሮ ውድነት፣ ለጤና ጠንቅ ለሆኑ ሸቀጦች እና ጥራት በጎደላቸው ሸቀጦች ጤናው እየታወከ ይገኛል። ከሁሉም በላይ በሸማቹ፣ በሻጩና በመንግሥት መካከል ያለው ግንኙነት የተዛባ፣ ኢፍትሐዊና ኢዴሞክራሲያዊ መሆኑ በተለይ ሸማቹን ሁልጊዜ ተበዳይ፣ ተገፊና ተጠቂ አድርጎታል። ይህን የተዛባ ግንኙነት የሚያስተካክልና የተነጠቀውን መብትና ያጣውን ጥቅም የሚያስመልስ አደረጃጀት ያስፈልጋል። በተለይ ወደ ንግድና ቀጣናዊ ትስስር የታጠፈው የንግድ ውድድርና የሸማች ባለስልጣን ራሱን ችሎ ሊደራጅ ይገባል።

የንግድና የግብይት ሥርዓቱን የሚቆጣጠረው ይህ ባለስልጣን ራሱን ችሎ ሊጠናከር ሲገባው በሚኒስቴሩ ስር መሆኑ የጥቅም ግጭት ይፈጥራል። ኢትዮቴሌኮምንና የኮሙኒኬሽን ባለስልጣንን በአንድ የማደራጀት ያህል ነው። ሆኖም የኑሮ ውድነቱ ጉዳይ ከአደረጃጀት ያለፈ አንገብጋቢ ችግር ስለሆነ ችግሩን እያነሳን ከማለቃቀስ ወደ መፍትሔው ማምራት ግድ ይላል።

መንግሥት በየደረጃው ከፍተኛ ቁጥር ያለውን ሸማች መብቱንና ጥቅሙን ለማስከበር ጥረት ቢያደርግም በሚፈለገው ደረጃ ውጤታማ ሊሆን አልቻለም። ላለፉት 30 አመታት በአገራችን ሲንከባለል የመጣውና ተባብሶ የመጣውን ከፍተኛ የዋጋ ግሽበትና የኑሮ ውድነት ተፈጥሯል። መንግሥት ዜጋውን በእጅጉ እየፈተነ ያለውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት ያደረጋቸው ጥረቶችም የሚፈለገውን ያህል ውጤታማ መሆን ባለመቻላቸው ከኢኮኖሚያዊ አጀንዳነት አልፎ የህልውና የሰላም የደህንነትና የጸጥታ ስጋት ወደመሆን እየዳኸ ይገኛል።

ስለሆነም የኑሮ ውድነቱና የዋጋ ግሽበቱ በጊዜ መፍትሔ ካላገኘ የሰላም የደህንነትና የጸጥታ አገራዊ ችግር የመሆን አቅም እንዳለው በመግባባት ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኝና በቅንጅት መረባረብ እንዲቻል አገራዊ ምክክር እንዲካሄድ ጸሐፊው ይመክራል።

የዚህ አገራዊ ምክክር ዐቢይ ዓላማ የኑሮ ውድነቱንና የዋጋ ግሽበቱን አንገብጋቢና አገራዊ የህልውና ጉዳይ መሆኑን ለመንግሥት ለሕዝብና ለተቋማት በማስገንዘብ የጋራ የመፍትሔ ፍኖተ ካርታ አዘጋጅቶ ወደ ተግባር የሚመራ ሲሆን፤ በምክክሩ የኑሮ ውድነቱም ሆነ የዋጋ ግሽበቱ ከኢኮኖሚ ችግርነት ባሻገር የህልውና ጉዳይ መሆኑን በመገንዘብ የአጭር የመካከለኛና የረጅም ጊዜ የመፍትሔ ሀሳቦችን ቀምሮ ፈጻሚያቸውን በመለየት ቆጥሮ ወደትግበራ መግባት ነው። አፈጻጸማቸውን በዚሁ የምክክር መድረክ በተሰየመ ጉባኤ ይገመገማል። አቅጣጫ ይሰጣል። ይመራል። የምክክር አጀንዳዎች ሊዳብሩና ሌሎች ርዕሶችን ማካተት ቢችሉም ጸሐፊው ለመነሻነት የሚከተሉትን አጀንዳዎች አቅርቧል።

**የምክክር አጀንዳዎች፡-**

ሀ. የኑሮ ውድነቱና የዋጋ ግሽበት ወቅታዊ ሁኔታና በሕዝብ በመንግሥትና በተቋማት ላይ የፈጠረው ከፍተኛ ጫና ፤

ለ .ግልፅ አቅጣጫ ተቀምጦ በተቀናጀ ርብርብ ኢኮኖሚያዊ ቀውሱ ካልተፈታ ወደ የሰላም፣ የህልውና፣ የደህንነትና የጸጥታ ችግር የመባባስ ስጋት መደቀኑ፤

ሐ. ከመድረኩና ከተሳታፊዎች የተቀመረ የጋራ የመፍትሔ ሀሳቦችን ማመላከትና መቀመር፤

**የመነሻ ሀሳብ አቅራቢ፤**

በሀ እና ለ የተመለከቱ አጀንዳዎችን በተመለከተ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ወይም የአአዩ ወይም የማህበራዊ ጥናት መድረክ የመነሻ ሀሳብ ወይም ጥናት ሊያቀርቡ ይችላሉ።

**በአገራዊ ምክክሩ የሚሳተፉ፤**

በአገራዊ ምክክሩ ይሳተፋሉ ተብሎ ከሚጠበቁ ባለድርሻ አካላት መካከል የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር፣ የፋይናንስ ሚኒስቴር፣ የፕላን ኮሚሽን፣ ጠቅላይ ዓቃቤ ሕግ፣ የጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት፣ ማህበራዊ ጥናት መድረክ፣ ማይንድ ኢትዮጵያ፣ የፌዴራል የሸማቾች ህብረት ሥራ፣ የአአ ከንቲባ ጽ/ቤት፣ የአአ ንግድ ቢሮ ፣ የንግድ ም/ቤት፣ የሃይማኖት ተቋማት ጉባኤ፣ የሚዲያ ካውንስል፣ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ማህበር ፣ የእንባ ጠባቂ ኮሚሽን ፣ የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ፣ የኢትዮጵያ ሸማቾች መብት ተቆርቋሪ ድርጅት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ም/ቤት፣ የሸማቾች ባለስልጣን፣ የሸማቾች ሕብረት ሥራ ማህበራት ፣ የጋዜጠኞች ማህበር ፣ ማህበራዊ አንቂዎች፣ ፌዴራል ፖሊስ፣ አዲስ አበባ ፖሊስ፣ ተስፋ ለኢትዮጵያ የሸማቾች ማህበር፣ ወዘተረፈ ይገኙበታል። የተሳታፊዎች ብዛት የሚዲያ ሰዎችን ጨምሮ ከ500-600 ሊደርስ ይችላል። የዚህ አገራዊ ምክክር አዘጋጆች የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚ/ር፣ የኢትዮጵያ ሸማቾች መብት ተቆርቋሪ ድርጅት፤ የፍሬደሪክ ኤበርት ስቲፍተንግ ኢትዮጵያ፤ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር፣ የኢፌዴሪ ሰላም ሚ/ር እና አጋሮቹ ጋር በመተባበር ሊሆን ይችላል።

የዚህ አገራዊ ምክክር ግብ የኑሮ ውድነቱም ሆነ የዋጋ ግሽበቱ የህልውና አደጋ ወይም የሰላምና የደህንነት ስጋት ሊሆን እንደሚችል በመንግሥት በሕዝብና በተቋማት መግባባት ላይ በመድረስ ለመፍትሔው አገራዊ ንቅናቄን በአዲስ አበባ ማስጀመር ሲሆን ይህን ተሞክሮና መድረክ ቀምሮ በሁሉም ክልሎችና በሁለቱ የከተማ አስተዳደሮች እስከ ወረዳ በማስፋት ግንዛቤና አደረጃጀት ፈጥሮ ቀጣይነትና ተከታታይነት ያላቸውን ተግባራት በማከናወን ተቋማትን በተለይ ሸማቹን በግብይት ሥርዓቱ የወሳኝነት ሚና እንዲኖረው/ empower/ ማድረግ ነው። ስለመፍትሔው ይሄን ያህል የመነሻ ሀሳብ ካቀረብሁ፤ ስለኑሮ ውድነቱ አሳሳቢነት ደግሞ ከተለያዩ ምንጮች የቀራረምሁትን አሁናዊ መረጃ ላጋራ።

ልክ እንደ ሌሎች አገሮች ሁሉ የኑሮ ውድነትና የዋጋ ግሽበት በኢትዮጵያም ማሳሰብ ከጀመረ ከራርሟል። የኑሮ ውድነቱ መነሻ በርካታ መንስዔ ያለው ችግር እንደሆነ ይነገራል። በመፍትሔነትም በርካታ ጉዳዮች ታሳቢ ሊደረጉ እንደሚገባ ማሳሰቢያ ሲቀርብ ይታያል። ለረዥም ዓመታት ሳያቋርጥ የቀጠለው የዋጋ ግሽበት የኑሮ ውድነትን እየወለደ በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ፣ ውጤቱ ወዴት ያመራል የሚለው ጉዳይ ደግሞ አሳሳቢነቱ የጎላ መሆኑ ተደጋግሞ ይነገራል ይለናል በአማርኛው ሪፖርተር ላይ የወጣ ዘገባ ።

ከሰሞኑ በተለይ በስንዴና በጤፍ ላይ የተፈጠረው የዋጋ ንረትና መናጋት፣ በኢትዮጵያ ያለውን የኑሮ ውድነት ምንጭና ምን ሊደረግ ይገባል ስለሚለው ጉዳይ ብዙ እያወያየ ይገኛል። በኢትዮጵያ የሚታየው የኑሮ ውድነት ወይም የዋጋ ንረት ጤናማ ያልሆነና ኢኮኖሚያዊ መነሻ የሌለው ነው የሚል አስተያየትም ይሰማል። የዋጋ ንረቱና የኑሮ ውድነቱ ከዚህ ቀደምም ቢሆን በንግድ አሻጥርና በሕገወጥ ግብይት የመጣ ነው የሚል አመክንዮ ሲያሰጥ ቆይቷል።

“The Ethiopian Economist View” በሚባለው የፌስቡክ፣ የቴሌግራምና የዩቲዩብ ገጽ ላይ የተለያዩ የኢኮኖሚ ጉዳዮችን በመተንተን የሚታወቁት የምጣኔ ሀብት ባለሙያ አቶ ዋሲሁን በላይም፣ የኑሮ ውድነቱ በኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ምንጭ አለው የሚለውን ሐሳብ ይጋሩታል።"የፖለቲካዊ ለውጦች ፍላጎትን ይጨምራሉ። ለምሳሌ በግጭትና በጦርነት የተነሳ ሰዎች ይፈናቀላሉ። እንዲሁም ከአምራችነት ወደ ምርት ፈላጊነት ሕይወታቸው ይቀየራል።

ይህ ደግሞ የምርት ፈላጊ ቁጥርን ስለሚጨምር ዋጋን ያሻቅባል። "የከተሞች ማደግ፣ የመንደሮች መስፋፋትና የመንገድ ትራንስፖርት እንቅስቃሴ መጨመር የባጃጅ ትራንስፖርት አቅርቦትን አስፈላጊ አድርጎታል። በየቦታው፣ በየጉምሩክ መፈተሻ ኬላውና በየወደቡ አላስፈላጊ ቀረጥና ታሪፍ መጨመርም ዋጋን ያንራል። ዕቃ ከውጭ ለማስገባት ታሪፍና ቢሮክራሲ ሲበዛ ዞሮ ዞሮ ሸማች ላይ ይመጣል። መሬት፣ መብራት፣ ውኃ፣ መንገድ ለማግኘት አምራቹ ዋጋና ቢሮክራሲ ሲበዛበት ችግሩ ተመልሶ ሸማቹ ላይ ይወድቃል፤"

አቶ ዋሲሁን እንደሚሉት፣ ወትሮም 40 በመቶ ላይ ብቻ ተወስኖ የቆየው የኢትዮጵያ አምራች ኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም፣ በተለያዩ ፖለቲካዊ ዕርምጃዎች የሚስተጓጎል ከሆነ የምርት አቅርቦት ችግርን የበለጠ ይጎዳል። አምራቾች የመጨረሻው የሸማች ኀብረተሰብ ላይ የሚያወርዱት ዋጋ የማምረቻ ወጪንና ትርፍን ብቻ ሳይሆን፣ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ያልሆኑ ጉዳዮችንም ታሳቢ ያደረገ መሆኑን ይገልጻሉ። የኃይል አቅርቦት፣ የብድር አቅርቦት፣ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ብቻ ሳይሆኑ የሠለጠነ የሰው ኃይል የማግኘት፣ እንዲሁም የተቀላጠፈ ቢሮክራሲያዊ አሠራር የማግኘት፣ አስተማማኝ የመሠረተ ልማት አቅርቦት ብቻ ሳይሆን አስተማማኝ ፀጥታና የደኅንነት ዋስትና የማግኘት አመቺነትንም ታሳቢ በማድረግ፣ አምራቾችና አቅራቢዎች ሸማቹ ኀብረተሰብ የሚከፍለውን ዋጋ እንደሚተምኑ አስረድተዋል።

በኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ አሶሴሽን ከፍተኛ ተመራማሪ የሆኑት አረጋ ሹመቴ (ዶ/ር) በበኩላቸው፣ አገሪቱ ያለችበት ሰላማዊ እንቅስቃሴ ስንዴን ወይም ጤፍን ከቦታ ወደ ቦታ አጓጉዞ ለመሸጥ አመቺ መሆን አለመሆኑም ዋጋውን እንደሚበይን ይናገራሉ። ምርት አለ ተብሎ በሚታመንበት ወቅት እንኳን ምርት ከገበያ የሚታጣውና ዋጋው የሚንረው በአገሪቱ ሰላምና ፀጥታ ሁኔታ ችግር መሆኑንም ያሰምሩበታል።"አገሪቱ ባለሁለት አኃዝ የዋጋ ግሽበት ማስተናገድ ከጀመረች 20 ዓመታት አስቆጠረች። ይህ የዋጋ ግሽበት ደግሞ ከሥራ አጥነት፣ ካልተረጋጋ የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ከውጭ ምንዛሪ እጥረትና ከውጭ ንግድ ሚዛን መዛባት ከመሳሰሉ ዓበይት የኢኮኖሚ ቀውሶች ጋር ሲደራረብ ችግሩን ያከፋዋል፤"በማለት ለጋዜጣው ይናገራሉ።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው አቶ ዋሲሁን፣ «የኑሮ ውድነት የዋጋ ንረትና የሰዎች የመግዛት አቅም መዳከም ተደምረው የሚፈጥሩት ችግር ነው፤» ይሉታል። የዋጋ ንረቱ መነሻ በቀጥታ ከፍላጎት መጨመር ጋር የተገናኘ መሆኑን የሚጠቅሱት ባለሙያው፣ የዜጎች ተጨማሪ ገቢ የማግኘት ዕድል የጠበበ ከመሆኑ ጋር ተዳምሮ ችግሩ መከፋቱን ያስረዳሉ። «ለአንዳንዶች የጤፍ በኪሎ ግራም አንድ መቶ ብር መግባትና ብዙም ሳይቀንስ ተሰቅሎ መቅረት ጉዳያቸው ላይሆን ይችላል። ከጤፍ ይልቅ የሱዙኪ ተሽከርካሪ ዋጋ መውጣትና መውረድ የሚያሳስባቸው አሉ። ይሁን እንጂ ገበያው በየቀኑ ሰዎችን እየተፋቸው፣ የመኖር ዋስትናን እያናጋ፣ ብዙ ሰውም በረንዳ እየወጣ በየቀኑ እያየን በመሆኑ፣ ችግሩ ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን ፖለቲካዊ መፍትሔዎችን የሚሻበት ደረጃ ላይ እንገኛለን፤» ብለዋል።

**ሻሎም ! አሜን ።**

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## የሴቶችን የዲጂታል እውቀትና ክህሎት ለማሳደግ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ቴክኖሎጂ በዓለም ላይ እየተስፋፋ ቢሆንም ሁሉንም ማህበረሰብ አካታች በማድረግ ረገድ ክፍተቶች እንዳሉ ግን ይነገራል። በዚህ ዘመን ለሰው ልጆች የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በእጅጉ አስፈላጊ የሆነው በይነመረብ (ኢንተርኔት) በዓለም አቀፍ ደረጃ በሚፈለገው መጠን ተደራሽ እንዳልሆነ መረጃዎች ያመለክታሉ። በአዲስ አበባ በተካሄደው 17ኛው ዓለም አቀፍ የበይነ መረብ ጉባኤ ላይ እንደተጠቆመው፤ በዓለም 2ነጥብ 7 ቢሊዮን፤ በአፍሪካ ደግሞ 871 ሚሊዮን ሕዝብ ከኢንተርኔት ግንኙነት ውጭ ነው።

በኢትዮጵያም የበይነ መረብ ተደራሽነት ከጊዜ ወደ ጊዜ መሻሻሎችን እያሳየ መሆኑን ነው በዚሁ ጉባኤ ላይ የተገኙት ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ አስታውቀዋል። በኢትዮጵያ ያለው የበይነ መረብ ተጠቃሚዎች ቁጥር ከአምስት ዓመት በፊት ከነበረበት 19 ሚሊዮን በአሁኑ ወቅት ከ30 ሚሊዮን በላይ መድረሱንም ተናግረዋል።

የዓለማችን ግማሽ ያህሉ ሕዝብ ከኢንተርኔት ውጪ እንደሆነም ይገለጻል። ከዚህ ውስጥ አብዛኛውን ቁጥር የሚይዙት ደግሞ የታዳጊ አገሮች ሴቶች መሆናቸው እየተጠቆመ ይገኛል።

የዲጂታል ዘርፉ የሰው ልጆችን የዕለት ተዕለት ሕይወት በማቅለል ረገድ ትልቅ ሚና አለው። በተለይም ጫና የሚበዛበትን የሴቶች ኑሮ ቀላል በማድረግ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ ያስችላል ተብሎ ይታሰባል። በዛሬው የ‹‹ሳይንስና ቴክኖሎጂ›› አምድ ዳሰሳችን በዲጅታሉ ዘርፍ በፆታ እኩልነት ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን ለማጥበብ እየተሰሩ ስላሉ ሥራዎች ያዘጋጀነውን ጥንቅር ይዘን ቀርበናል።

በቅርቡ ‹‹ዲጂታል ለሁሉም›› (Digital for All) በሚል ርዕስ ዓለም አቀፍ የሴቶች ቀን በአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን/ኢሲኤ/ አዳራሽ በተከበረበት ወቅት፤ አካታች የዲጂታል ምጣኔ ሀብትን እውን ለማድረግ እውቀትና ክህሎት ላይ ትኩረት ተደርጎ መሥራት እንዳለበት ተገልጿል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዴኤታ ሁሪያ አሊ እንዳሉት፤ ዲጂታል ቴክኖሎጂ ሕይወትን ቀልጣፋ፣ ቀላልና ምቹ እንዲሆን አድርጓል። በትምህርት፣ በጤናና በሌሎች ዘርፎች ላይ ሕይወት ቀላልና ምቹ እንዲሆን የሚያስችሉ ሁኔታዎች እየፈጠረ ነው።

በቴክኖሎጂው ተጠቃሚ በመሆን በኩል ግን በጾታ ልዩነት እንዳለ ነው የተጠቆመው፤ የሴቶች የቴክኖሎጂው ተጠቃሚነት ከወንዶች ጋር ሲወዳደር ዝቅተኛ ነው። ለዚህም ምክንያቱ ዲጂታል ቴክኖሎጂን ለመጠቀም ትምህርት ወይም ክህሎት አስፈላጊ በመሆኑ ነው።

እንደ አገር በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው ልዩነት ሴቶች በዲጂታሉ ዓለም ላይ የሚመጡትን ቴክኖሎጂዎች በተፈለገው መጠን እንዳይጠቀሙ እያደረገ ነው። ለዚህም ትልቁ ማነቆ የዲጂታል ክህሎትና እውቀት ማነስ ነው ይላሉ።

‹‹በኢትዮጵያ ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት ከተለዩ አንኳር ችግሮች ውስጥ የዲጂታል ክህሎትና እውቀት ማሳደግ አንዱ ነው›› የሚሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ሴቶች የዲጂታል ክህሎትና እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ በርካታ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውንም ነው ያስታወቁት።

እሳቸው እንደሚሉት፤ ሴቶችን የዲጂታል ክህሎትና እውቀት እንዲኖራቸው ማስተማር ይገባል። ከዚያ በኋላ የሚመጡትን ቴክኖሎጂዎች እንዲጠቀሙ በማድረግ ሴቶች ለኢኖቬሽን፣ ለቴክኖሎጂና ለዲጅታላይዜሽን የቀረቡ እንዲሆኑ መሥራት ያስፈልጋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ ጥናቶች ጠቅሰው እንደተናገሩት፤ ሴቶች ለኢኖቬሽን፣ ለቴክኖሎጂና ለዲጂታላይዜሽን የቀረቡ ናቸው። ይህንን እድል እንዲጠቀሙ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

‹‹ሴቶች ለአዳዲስ ፈጠራዎች ቅርብ ስለሆኑ እውቀት ቢጨመርላቸው ቴክኖሎጂውን እንዲጠቀሙና እንዲፈጥሩ ያግዛቸዋል፤ የቴክኖሎጂ ፈጣሪዎች ይሆናሉ›› የሚሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ አሁን ላይ ሴቶች በዲጂታሉ ዘርፉ እየተሳተፉ ትላልቅ ቴክኖሎጂዎችን እየፈጠሩ እንደሆነም ይናገራሉ። አገራችንም የዚህ ቴክኖሎጂ ተቋዳሽ



እንድትሆን በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በኩል በዲጂታል ልዩነት ላይ የተለያዩ ሥራዎች እየተሰሩ እንደሚገኙ ጠቁመዋል።

የዲጂታል እውቀት ልዩነቱ በወንድ እና በሴት፣ በከተማ እና በገጠር እንዲሁም በወጣቶችና በአረጋውያን መካከል ያለ መሆኑን ጠቁመው፤ መጠኑ የሚሰፋው ግን በሴቶችና በወንዶች መካከል ያለው ልዩነት እንደሆነ ይናገራሉ። ልዩነቱን ለማጥበብ እንደ አገር ጥናት እየተካሄደ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ በጥናቱ ግኝት መሰረት ስትራቴጂ በመቅረጽ ሴቶችን ተጠቃሚ ለማድረግ ይሰራል ብለዋል።

እንደ ሚኒስትር ዴኤታዋ ገለጻ፤ በአገር ደረጃ በዲጂታል ኢኮኖሚ ተጠቃሚነት ረገድ ከተሰሩ ሥራዎች አንዱ የቴሌኮም ዘርፉን ለገበያ ተወዳዳሪ ማድረግ ነው። ይህም በሴቶች እኩልነት ላይ ትልቅ አስተዋፅኦ አለው። የዲጂታል ተደራሽነትን በማስፋት ሴቶችን ተጠቃሚ ማድረግ ያስፈልጋል።

በኢኖቬሽን፣ በቴክኖሎጂና በዲጂታላይዜሽን ዘርፍ የጾታ እኩልነት እንዲኖር አካታች የሆነ ማህበረሰብን ለመፍጠር እየተሰራ መሆኑንም ጠቅሰው፣ ለዚህም የጾታ እኩልነትን የተመለከተ ፖሊሲ በመቅረጽና ስትራቴጂ በመንደፍ በርካታ ሥራዎች እየተሰሩ መሆኑን አመላክተዋል።

እሳቸው አንደተናገሩት፤ እ.ኤ.አ በ2017 የተደረገ ጥናት እንደሚያሳየው የባንክ አካውንት ካላቸው ከአምስት ሰዎች መካከል አንዷ ብቻ ሴት ናት። ለዚህም የመታወቂያ አለመኖር በምክንያት ይጠቀሳል። አነስተኛ ገቢ ካላቸው አገራት 45 በመቶ የሚሆኑት እድሜያቸው ከ15 ዓመት በላይ የሆነ ሴቶች ሕጋዊ መታወቂያ የላቸውም ይላሉ።

ዲጂታል መታወቂያ የጾታ እኩልነትን የሚያሳይ መሆኑን ጠቁመው፤ ይህም አካታች ዲጂታል መታወቂያ ስርዓት በመዘርጋቱ ሴቶች ሕጋዊ የመታወቂያ አገልግሎት እንዲያገኙ ሰፊ እድል ይፈጥርላቸዋል ይላሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ በኢትዮጵያ የሴቶች የዲጂታል እውቀት ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር እጅግ አነስተኛ ነው። በቴክኖሎጂና በዲጂታላይዜሽን ዘርፍም ሴቶች ያላቸው ተሳትፎ አነስተኛ ሆኖ ይታያል። ተሳትፏቸው አነስተኛ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች መካከል፣ የዲጂታል እውቀትና ክህሎት ማነስ ይጠቀሳሉ።

እነዚህን ችግሮች በመቅረፍ በሴቶችና በወንዶች መካከል እኩል የሆነ ሶሾዮ ኢኮኖሚ መፍጠር ያስፈልጋል ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ የሴቶች የዲጂታል ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እንዲሻሻል ለማድረግ የሴቶችን የቴክኖሎጂ አቅም ለማሳደግ የሚያስችል ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል ብለዋል።

የኢትዮጵያ መንግሥት የዲጂታል ዘርፉን ለማሻሻል የአምስት ዓመት ስትራቴጂ ቀርጾ ተግባራዊ እያደረገ እንደሚገኝ ተናግረው፣ በተጨማሪም አዳዲስ የዲጂታል አገልግሎት ለሚሰጡ አካላት በሩ ክፉት መደረጉን ሚኒስትር ዴኤታዋ ያመለክታሉ፤ የፋይናንስ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት የዲጂታል ፋይናንስ አገልግሎቶች መስጠት ለመጀመራቸው ቴሌ ብር አንዱ ማሳያ መሆኑን ይጠቅሳሉ።

አካታች የዲጂታል ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት እየተካሄደ መሆኑን ጠቁመው፤ ጥናቱ የዲጂታል ፋይናንሺያል ክህሎት ክፍተትን በመለየት በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ለመስጠት እንደሚያስችል ገልጸዋል። ‹‹ዲጂታል ኢኮኖሚን ከዲጂታል እውቀትና ክህሎት ውጪ ማሰብ የማይቻል ›› ያሉት ሚኒስትር ዴኤታዋ፤ ለዚህም ከሚመለከታቸው አጋር አካላት ጋር አብሮ መስራት ያስፈልጋል ይላሉ።

‹‹ዲጂታል ዘርፉን መንግሥት ብቻውን ስለሰራ በዘርፉ የሚፈልገውን እውን ማድረግ እንደማይቻል ሚኒስትር ዴኤታዋ አስገንዝበዋል፤ ስራው የሁሉንም ተቋማት ርብርብ እንደሚጠይቅ ይገልጻሉ። በአገራችን ያሉ በዲጂታል ላይ ፍላጎት ካላቸው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (UN) እና ከሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት መሥራት አስፈላጊ መሆኑንም ተናግረዋል። በተለይ ሴቶች በዲጂታል ዘርፉ ላይ ያሉባቸውን ችግሮች ለመፍታት ከሌሎች አጋር ድርጅቶች ጋር በትብብር መስራት ይኖርባቸዋል ብለዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ ‹‹ከተቋማት ጋር አብረን ከሰራን ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 በአጭር ጊዜ እውን በማድረግ ዲጂታል ኢትዮጵያን መገንባት እንችላለን። ዲጂታል ኢትዮጵያን መገንባት ከቻልን ደግሞ አዳዲስ የሥራ እድሎችን መፍጠር ይቻላል፤ የውጭ ምንዛሬን መጨመር ይቻላል። አካታች የሆነ ዲጂታል ኢኮኖሚን እንደአገር መገንባት ይቻላል›› ሲሉ አስረድተዋል።

የሴቶች የዲጂታል ተሳትፎ በጣም አነስተኛ ነው የሚለውን ሀሳብ የሚጋሩት የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ዘርፍ ባለሙያው አቶ ሀብታሙ ዳምጤ በበኩላቸው፤ ‹‹የሴቶች ዲጂታል ተሳትፎ ያለበትን ደረጃ ለማወቅ ዓለምን እየመሩ ያሉ የማህበራዊ ሚዲያ ፕላትፎርሞች አሃዝ ብንመለከት እንኳን የሴት የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚዎች ቁጥር በጣም አነስተኛ መሆኑን መመልከት ይቻላል›› ይላሉ።

‹‹በተመሳሳይ የቴሌብር፣ የሞባይል ባንኪንግን ተጠቃሚ ሴቶችን ብንመለከት አሃዙ ስለሌለ እንጂ ከዚህ የተለየ ነው ማለት አያስደፍርም›› ሲሉ ገልጸው፣ ሴቶች በዲጂታል ዘርፉ ጎልተው እንዳይወጡ ካደረጉ ችግሮች መካከል ትምህርት ቤት ያለመግባት፣ ሥራ ላይ አለመሳተፍ፣ ወጥቶ መሥራት አለመቻል፣ የተደራሽነትና የግንዛቤ እጥረትን በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።

‹‹ለምንም ነገር መሠረት የሚጣለው ከታች ነው›› የሚሉት አቶ ሀብታሙ፤ ለአብነት ሴቶች መስሪያ ቤት የሚሰሩበት ሁኔታ ቢፈጠር ለዲጂታሉ ዘርፍ ቅርበት ይኖራታል፤ ከቴክኖሎጂ ጋር ግንኙነት ሊኖራት የሚችልበት አጋጣሚም ይፈጥራል ይላሉ።

አቶ ሀብታሙም በዲጂታል ዘርፉ የሴቶች የእውቀትና የክህሎት ክፍተት መኖሩን ይገልጻሉ። በተመሳሳይ በኢንተርኔት አጠቃቀምና ቴክኖሎጂ ላይ ሴቶች የአመለካከት ክፍተቶች እንዳሉባቸው ይናገራሉ። ማህበራዊ ሚዲያን ሀሰተኛ መረጃ የሚወራበትና ስህተት እንደሆነ ብቻ አድርጎ የመመልከት አመለካከት እንዳላቸውም ነው አቶ ሀብታሙ የሚጠቁሙት። በመሆኑም ብዙ ሴቶች ዘመናዊ ስልክ ይዘውና ኢንተርኔት መጠቀም የሚያስችል ሁኔታ ውስጥ ሆነው አንጠቀምም የሚሉበት ሁኔታ እንዳለ ይጠቅሳሉ።

‹‹ማህበራዊ ሚዲያን በመጠቀም ለሴቶች ብቻ ተብለው የሚለቀቁት ማስታወቂያዎች እንኳን ብንመለከት በጣም ውድ ናቸው›› የሚሉት አቶ ሀብታሙ፤ ለዚህም እንደምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ አንዱ የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚ ሴቶች ቁጥር አነስተኛ መሆን ነው።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ሳይንሱ እንደሚለው ሴቶች በቴክኖሎጂ እድገት ላይ በጣም ወሳኝና ቅርብ ናቸው። ወንዶች በሀርድ ዌር ማኑፋክቸሪንግ እንዲሁም ሴቶች ደግሞ ለሶፍት ዌር ኮዲንግና ለዌብ ሳይት ዲዛይን ተመራጭ ናቸው።

በዌብ ሳይት ዲዛይን የከለሪንግ እና ፈጠራ የሚጨመርባቸው ሥራዎችን ለመሥራት ሴቶች እንደሚመረጡ ተናግረዋል። አንድ መተግበሪያ ወይም ዌብ ሳይት ለማበልጸግ ኮድ መደረግ ስላለበት ኮድ ማድረግ ደግሞ ረጅም ሰዓት መቀመጥን ስለሚጠይቅ የሴቶች ባሕሪ ለዚህ የተመቸ ነው የሚሉት አቶ ሀብታሙ፣ ቴክኖሎጂን በማላመድ ረገድም ሴቶች በባንክ ሲስተሞች ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ዘርፎች ላይ ተመራጭ እንደሆኑም ይጠቁማሉ።

አቶ ሀብታሙ እ.ኤ.አ በ2023 የተካሄደ ጥናት ያመለከተውን ጠቅሰው ሲያብራሩም፤ ኮዲንግ (ኮምፒዮተር ፕሮግራሞች ላይ የሚሰሩ) ተሳታፊ ሴቶች 27 በመቶ ያህል መሆናቸውን ይናገራሉ፤ በኢትዮጵያ ደረጃ የሴቶች የኮምፒውተር ሳይንስ ትምህርት ተሳትፎ አነስተኛ መሆኑንም ጠቅሰው፣ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሴቶች የኮምፒዩተር ሳይንስ የትምህርት ክፍል ምርጫቸው እንዲያደርጉ ምክረ ሀሳብ ቢለገሱ ውጤታማ መሆን ይቻላል ሲሉም ይጠቁማሉ።

አቶ ሀብታሙ ‹‹የሴቶችን ዲጂታል ተጠቃሚነት የማጎልበቱ ተግባር ትኩረት ሰጥቶ መሥራትን ይጠይቃል። በሴቶች ላይ የሚፈጸሙ ሌሎች ተፅዕኖዎችን ማስቀረት የሚያስችሉ የተለያዩ ግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎች እንደሚሰሩ ሁሉ በዲጂታሉም ረገድ የሴቶችን ግንዛቤ በማሳደግ ውጤታማ ሥራ መስራት ይቻላል›› ሲሉ አስረድተዋል።

እንደ ጎግል፣ ፌስቡክ የመሳሳሉት ተቋማት ለሴቶች ብቻ እያሉ የሚያዘጋጇቸው ስልጠናና ሌሎች እድሎች እንዳሉም ገልፀው፤ ይህንን ወደ አገራችን በማምጣት ማስፋፋት ሴቶች ከቢዝነስና ቴክኖሎጂው ዘርፎች ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል ብለዋል።

ቀደም ሲል የኔትወርክ ፍጥነት፣ የዘመናዊ የስልኮች ተደራሽነት አለመስፋት እና ብዙ አይነት የገንዘብ ዋሌቶችና የመሳሰሉ ፕላትፎርሞች አለመኖር ወደኋላ ሲጎትቱን ቆይተዋል ሲሉ ጠቅሰው፣ እነዚያ ወደኋላ ሲጎትቱ የነበሩት ችግሮች መቀረፋቸውን ተናግረዋል፤ አሁን ላይ ያለው የግንዛቤ እጥረት መሆኑን ጠቅሰው፣ ሰዎች ላይ መሠራት አለበት። ግንዛቤ ላይ ከተሰራ ደግሞ ለውጥ በማምጣት ውጤታማ መሆን ይቻላል›› ይላሉ።

‹‹ኢንተርኔት ሁሉም ነገር መማሪያ ነው፤ ያለንን እውቀት ማሳደግ የሚቻልበት ነው›› የሚሉት አቶ ሀብታሙ፤ ቴክኖሎጂ የሰው ልጆችን የዕለት ከዕለት ሕይወት ቀላል የሚያደርግ በመሆኑ ሴቶች ለቴክኖሎጂ ቅርብ ከመሆናቸው አንጻር ቢጠቀሙ ራሳቸውን ተጠቅመው ለአገርም ይጠቅማሉ ብለዋል። ሴቶች የራሳቸውን ቢዝነስ ለመስራት፣ ያለባቸውን የሥራ ጫና ለማቅለል፣ የአኗኗር ዘይቤያቸውን ከቴክኖሎጂ ጋር በማስተሳሰር ቀላል ለማድረግ ቢችሉ መልካም ነው ሲሉ ይመክራሉ።

# ወቅታዊ ትንታኔ

## መነቃቃት የታየበት የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት…

ክብረአብ በላቸው



አቶ ክቡር ገና



ዶክተር ዘላለም እጅጉ

የአንድን አገር ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እድገት ከሚወስኑ አበይት ጉዳዮች መካከል በአገሪቱ ውስጥ የሚካሄደው የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ትልቁን ድርሻ ይወስዳል:: ኢንቨስትመንት ለአንድ አገር እድገት ያለው ጠቃሜታ ዘርፈ ብዙ ነው:: ለዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ከማስቻሉም በላይ የውጭ ምንዛሬ ምንጭም በመሆን አገርን ከዶላር እጥረት ይታደጋል::

የውጭ ኢንቨስትመንት ለአገሪቱ ልማት ተገቢውን አስተዋፅኦ እንዲያበረክት ማድረግ እና በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ በማደግ ላይ ባሉ አገራት ኢንቨስትመንት የሥራ ዕድልን በመፍጠር እና የቴክኖሎጂ ሽግግር በማምጣት ሰፊ ሚና ይጫወታል::

ባለፉት ሁለት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ በነበረው ጦርነት የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ዘርፍ እጅጉን ሲፈተን ቆይቷል፤ በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል ተከስቶ በነበረው ጦርነት ምክንያት ብሎም በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ዘርፉ ተዳክሞ ቆይቷል፤ በተለይ የኢትዮጵያ ትልቋ የውጭ የኢንቨስትመንት አጋር የሆኑት ቻይናን የመሳሰሉ አገራት በኮቪድ መጠቃታቸው በተዘዋዋሪ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ላይ የራሱን የሆነ ጫና አሳድሯል::

ስለዚህም ያለፉት ሁለት አመታት ለኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ፈታኝ ጊዜዎች ነበሩ:: በችግሩ ልክ ጠንካራ ሥራዎችን ለመሥራት ታቅዶ ወደ ተግባር በመቀየሩ ባጋጠመው ቀውስ ልክ ውድቀት እንዳይኖር ለማድረግ እንደተቻለ እና ምንም እንኳ የሚጠበቀውን ያህል ውጤታማ ለመሆን ባይቻልም ችግሮችን ተቋቁሞ ለማለፍ ጥረት እንደተደረገ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በተለያዩ ጊዜያት ሲገልፅ ቆይቷል:: በ2014 ዓ.ም ኢትዮጵያ 3 ነጥብ 31 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት አስመዝግቦ የነበር ሲሆን፣ ይህም በምሥራቅ አፍሪካ ቀዳሚዋ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የሳበች አገር አድርጓታል፤ በአጠቃለይ በአህጉር አቀፍ ደረጃ ደግሞ ሦስተኛ ደረጃ ይዛለች:: ይህም በብዙ ፈተና ውስጥ መልካም የሚባል ውጤት መመዝገቡን የሚያሳይ ነው::

በያዝነው ዓመት ስድስት ወራት ውስጥ 2 ነጥብ 95 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ታቅዶ ወደ 1 ነጥብ 9 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ እንደተቻለ ይህም የዕቅዱን 64 ከመቶ እንደሆነ የፕላን እና ልማት ሚኒስቴር ገልጿል፤ ይህም ከባለፈው ተመሳሳይ ወቅት ጋር ሲነፃፀር 16 ነጥብ 3 በመቶ ብልጫ እንዳለው በማስታወስ፤ በቀጣይ 12 ወራት ደግሞ 6 ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ለማምጣት ታቅዷል፤

በ2015 የበጀት ዓመት የሰሜኑ ጦርነት በሰላም ስምምነት መቋጨቱ አወንታዊ ተፅዕኖ አምጥቷል፤ ከሰላም ስምምነቱ በኋላ ያሉ የኢንቨስትመንት ፍላጎቶች መጨመር እና የዓለም አቀፍ ጫና መቀነሱ ለዕቅዱ መሳካት ወሳኝ እንደነበር ተገልጿል:: አገሪቱ በግጭት እንደመቆየቷ የተመዘገበው ውጤት ይበል የሚያሰኝ እንደሆነ የኢኮኖሚ ባለሙያዎች ይገልፃሉ::

ለማክሮ ኢኮኖሚው ትልቅ አቅም እንደሚሆን የሚጠበቀው የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት የተለያዩ ተግዳሮቶች ቢኖሩበትም ችግሮችን እየተቋቋመ ተጨማሪ ውጤቶችን ማስመዝገብ እንደሚጠበቅበት የስድስት ወራት ዋና ዋና የማክሮ ኢኮኖሚ የዘርፎች ዕቅድ አፈፃፀም በተገመገመበት ወቅት የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ተናግረዋል::

ይህንኑ ጉዳይ በተመለከተ የዘርፉ ምሁራን ሃሳብ አላቸው:: የኢኮኖሚ ባለሙያው አቶ ክቡር ገና እንደሚናገሩት፤ ለኢንቨስትመንት መነቃቃቱ ትልቅ አስተዋጽኦ ያደረገው የጦርነቱ መቆም ነው። ጦርነት ባለበት ሁኔታ የውጭ ኢንቨስትመንት ይመጣል ተብሎ የሚታሰብ አይደለም፣ ጦርነት መቆሙ ከዚህ በፊት ኢንቨስት ለማድረግ የፈለጉ እና በጦርነቱ ምክንያት ኢንቨስትመንቱን ለጊዜው ያዝ ያደረጉ አገራት እና ኩባንያዎች ወደ ኢንቨስትመንት ለመግባት የቻሉበት ሁኔታ አለ፣ ከዚህ ውጪ መንግሥት ያስተካከላቸው ሁኔታዎችም አሉ፣

በተለይ የውጭ ኢንቨስተሮች እንዲመጡ ብዙ ጥረት መደረጉ ለውጦች እንዲመጡ አስችሏል:: በየአገሩ ጉብኝት እየተደረገ ስለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መከፈት እና በተለይ ደግሞ የጦርነቱን መቆም አስታኮ ለበርካታ ካምፓኒዎች ኢንቨስት እንዲያደርጉ ተጋብዘዋል:: ከጅቡቲ ጀምሮ፣ ወደ መካከለኛ ምሥራቅ ያሉትን ኢንቨስተሮች የበለጠ ለመሳብ ጥረት ተደርጓል የዚህ ውጤት ነው አሁን የተሻለ ለውጥ ያሳየው ብለዋል።

ሆኖም የተነቃቃው ኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ እንዲጠናከር መሻሻል አለባቸው ያሏቸውን ነጥቦች አቶ ክቡር ገና አስቀምጠዋል:: ለኢንቨስትመንቱ ዋና አጋዥ የሆነው የኃይል አቅርቦት ሳይቆራረጥ በመደበኛነት መቅረብ አለበት:: የመሬት አቅርቦቱንም ማስተካከል ያስፈልጋል:: የተጀመሩ የመሠረት ልማት ሥራዎች በፍጥነት መጠናቀቅ አለባቸው:: የውጭ ምንዛሬ ሁኔታዎች መስተካከል ይኖርባቸዋል:: በእነዚህ ሁኔታዎች በመጠኑም ቢሆን መንግሥት እየሠራበት ቢሆንም ቶሎ ቶሎ በፍጥነት መስተካከል እንደሚኖርባቸው ተናግረዋል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው እና በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል መምህሩ ዶክተር ዘላለም እጅጉ በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ ያለው የውጭ ኢንቨስትመንት መነቃቃት ወደኋላ መለስ ብሎ ማየት ያስፈልጋል ይላሉ:: ከመንግሥት ለውጡ ማግስት የተወሰኑ መነቃቃቶች ነበሩ፤ ከዚያ በኋላ ግን የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ተፅዕኖ ደግሞ ወደኋላ እንዲመለስ አድርጎታል፤ ከዚያ በኋላ በመንግሥት የተለያዩ ጥረቶች ተደርጓል:: ከኮቪድ 19 ወረርሽኝ ቀስ በቀስ በማገገምም የኢንቨስትመንት ፍሰቱ ውጤት ማሳየት ችሏል ብለዋል::

ለዚህም ምክንያቶቹም የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት አስፈላጊነቱን መንግሥት በማመኑ በተለይ የሥራ ዕድል ለመፍጠር እና ድህነትን ለመቀነስ እንደ ፖሊሲ መያዙ እና የመንግሥት ቁርጠኝነት መኖሩ፤ ሁለተኛው ነገር ከፖሊሲ ማሻሻያው ጋር ተያይዞ የመጣው የቴሌኮሙኒኬሽንን ለግል ባለሀብቶች ፍቃድ መስጠቱ በራሱ ወደ 860 ሚሊዮን ዶላር የሚሆን የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ገቢ እንዲሆን አስችሏል ብለዋል::

ሌላው ነገር ደግሞ የኢንዱስትሪ ፓርኮች መቋቋም በተለይ የይርጋለም አግሮ ኢንዱስትሪ፣ ሀዋሳ፣ እና ሌሎችም የኢንዱስትሪ ፓርኮች ላይ የውጭ አልሚዎች በደንብ ወደ ሥራ መግባት መቻላቸው የወቅቱ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት ከፍተኛ እንዲሆን ወይም እንዲጨምር አስችሏል ይላሉ ዶክተር ዘላለም ::

እስካሁን ባለው የውጭ ኢንቨስትመንቶች ምንን መሠራት አድርገው ነው ወደ አገራችን የሚመጡት የሚለው ሲታሰብ ትልቁ ነገር በአፍሪካ ትልቅ የገበያ ዕድል መኖሩ ነው:: አፍሪካ ሁለተኛው የሕዝብ ብዛት ያለት አህጉር ናት፤ በተጨማሪም ወጣት ወይም አምራች የሰው ኃይል በብዛት መኖሩ ሌላው ሳቢ ምክንያት ነው:: ከዚህ በተጨማሪ በመንግሥት ፖሊሲ የኢንቨስትመንት ሕግ ላይ መነሻ ሊሆኑ የሚችሉ ማበረታቻዎች መካተታቸው እንደ አንድ ዕድል ሊታይ የሚችል ነገር ነው::

እንደምሁሩ ገለጻ በአስር አመቱ መሪ የልማት እቅድ የተካተቱ ቁልፍ የሆኑ ሴክተሮች አሉ :: በተለይ የውጭ ኢንቨስትመንት ለመሳብ የተደረጉ የማግባባት ሥራዎች ይበል የሚያሰኙ ናቸው:: ከዚያ በተጨማሪ እየተገነቡ ያሉ የኢንዱስትሪ ፓርኮች እና በመንግሥት በኩል ያለው የመሠረተ ልማት አቅርቦት ጥሩ ዕድል ነው ብለዋል::

ነገር ግን እነዚህን ዕድሎች በደንብ እንዳንጠቀም ያደረጉ ተግዳሮቶች መኖራቸውን ዶክተር ዘላለም እጅጉ ያብራራሉ:: አሁን ያሉ የፖለቲካም ሆነ የኢኮኖሚ አለመረጋጋቶች ትልቅ ተፅዕኖ ይፈጥራሉ:: ነባር ኢንቨስትመንቶች ደግሞ ተረጋግተው እንዳይቆዩ ትልቅ እንቅፋት ይሆናሉ:: ስለዚህ መንግሥት የሚጠበቅበት የተረጋገጠ ሰላም እና መረጋጋት እንዲኖር መሥራት ነው፤ የኢኮኖሚ መረጋጋት ስንል ከዋጋ ግሽበት፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት እና መሰል ከማክሮ ኢኮኖሚ ጋር የተያያዙ ነገሮች መቅረፍ መቻል ይኖርበታል ብለዋል::

ሌላው በቂ የማስፈፀም አቅም ያላቸው ተቋማት አለመኖር ወይም ደግሞ ያሉትም ቢሆኑ የማስፈፀም አቅም ውስንነት ችግር ያለባቸው መሆናቸው ነው፤ ጥሩ ጥሩ ሕጎች አሉ እነዚያን ሕጎች በአግባቡ መፈፀም አለመቻል ኢንቨስተሮች በራስ መተማመን እንዳይኖራቸው ያደርጋል፤ ኢንቨስትመንት ደግሞ መተማመን እና ተገማች የተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ ሲኖር ነው ጥሩ ውጤት የሚኖረው:: ሌላው በውጭ ኢንቨስትመንት ብድር አወሳሰድ ላይ ያሉ የማስፈፃም ክፍተቶች፣ ከውጭ የሚገቡ ማሽነሪዎች ውጤታማነትና በክልል መንግሥት እና በፌዴራል መንግሥት ያሉ የመሬት አቅርቦት ላይ ያሉ ውስንነቶችን መቅረፍ አስፈላጊ ነው:: መንግሥት እነዚህ ጉዳዮች ላይ ትኩረት አድርጎ ሊሠራ ይገባል ብለዋል::

ዶክተር ዘላለም በተጨማሪ ሲናገሩ፤ አገሪቱ ወደብ አልባ ከመሆኗ አንፃር ከፍተኛ የሆኑ ወጪዎች ይኖሩባታል:: በገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ የየብስ ትራንስፖርት ወጪውም ከፍተኛ ነው:: ከወደብ ወደ አገር ቤት ለመምጣት ደግሞ የቢሮክራሲ ችግር አለ፤ በቀላሉ ሊፈፀሙ የሚችሉ ነገሮች ብዙ የሥራ ቀናትን ይወስዳሉ፤ በጉምሩክ አካባቢ ያሉ የሙስና ድርጊቶች ለኢንቨስትመንቱ እክል ናቸው:: ስለዚህም የኢንቨስትመንት ፍሰቱ የተሻለ ደረጃ ላይ እንዲደርስ መንግሥት ያሉትን ዕጸጾች ማጽዳት ይጠበቅበታል ብለዋል::

ከዚህ በተጨማሪም በተለያዩ ምክንያቶች ኢትዮጵያ ያጣችውን ከቀረጥ ነፃ ወደ አሜሪካ ገበያ የመለክ ዕድል (አገዋ) መንግሥት ባደረገው የዲፕሎማሲ ጥረት የመነሳት ዕድል ስላለው ጥረቱን አጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል:: ይሄም ለውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንቱ ተጨማሪ መልካም አጋጣሚ እንደሚሆንም አብራርተዋል::

አቶ ክቡር ገና በበኩላቸው፤ አሁን ያለው ጥሩ ሁኔታ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ሰላም መቀጠል እንዳለበት ያሰምሩበታል:: የሰላም ሂደቱ ያዝ ለቀቅ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል፤ አለመግባባቶች ከመስመር ወጥተው ወደሌላ ችግር እንዳይወስዱን መጠንቀቅ ይገባል ብለዋል::

ሌላው የማስተዋወቅ ሂደቱ መቀጠል አለበት፤ ሌሎች ኢንቨስተሮችን የመፈለግ እና ኢንቨስተሩን ሊያረካ በሚችል መልኩ ሥራዎችን በቅልጥፍና እንዲሠራ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣ ደንቦችን ማስተካከል፣ ሕጎችን የበለጠ ለንግዱ በሚጠቅም መልኩ መከለስ ያስፈልጋል በማለት ሃሳባቸውን ቋጭተዋል::

**በገቢና ወጪ ዕቃዎች ላይ የየብስ ትራንስፖርት ወጪውም ከፍተኛ ነው:: ከወደብ ወደ አገር ቤት ለመምጣት ደግሞ የቢሮክራሲ ችግር አለ፤ በቀላሉ ሲፈፀሙ የሚችሉ ነገሮች ብዙ የሥራ ቀናትን ይወስዳሉ፤ በጉምሩክ አካባቢ ያሉ የሙስና ድርጊቶች ለኢንቨስትመንቱ እክል ናቸው**

ማህበራዊ

# ሴቶች


ብያና ዋኬና


እስካለች ቀነአ


ደሳለኝ ታፈሰ


ሲስተር ካሰች ለታ

# ሴቶችና ህፃናትን ለመታደግ ተስፋ የተጣለበት ስልጠና

ሰላማዊት ውቤ

በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ጉዳት ለደረሰባቸው ዜጎች የተለያዩ ድጋፎችን ማድረግ ለነገ የሚተው የቤት ስራ አይደለም:: ለነዚህ ዜጎች የሚደረጉ ድጋፎች የገንዘብ፣ ቁሳቁስ፤ እንዲሁም ማህበራዊ፣ ስነ ልቦናዊና አእምሯዊ ሊሆኑ ይችላሉ::በተለይም ሴቶችና ህፃናት በእንዲህ አይነት ችግሮች ውስጥ ሲገኙ ደግሞ ድጋፉ ፈጥኖ እንዲደርስ ማድረግ ግድ ነው::

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ከሰሞኑን በአዳማ መልካ አዳማ ሆቴል ይሄን ታሳቢ ያደረገ የአሰልጣኞች ስልጠና ሰጥተል:: ከመጋቢት 28 እስከ ሚያዝያ 7 ቀን 2015 ዓ.ም በዘለቀው የስልጠና መርሐ ግብር መክፈቻ ላይ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማህበራዊ ዘርፍ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ አየለች እሸቴ እንደተናገሩት፣ ስልጠናው ዘርፈ ብዙ ዓላማ ያለው ሲሆን በዋናነት የስነ ልቦና፤ የማህበራዊ እና የአእምሮ ጤና ድጋፍ አገልግሎቶችን ውጤታማነት ለማሳደግ የታሰበ ነው:: በዘርፉ የሚታየውን የእውቀትና የክህሎት ክፍተት እንደሚቀርፍ ጠቁመዋል:: የተቀናጀና በእውቀት ላይ የተመሠረተ የድጋፍ አገልግሎት መስጠት ያስችላልም ብለዋል:: ተቋማዊ አቅም ለመፍጠር ማለሙንም አንስተዋል:: ይህ ስልጠና የአቅም ማጎልበቻ ስልጠና ሲሆን በዋነኛነትም በጾታዊ ጥቃት ምላሽ አሰጣጥ፣ በአዕምሮ ጤና፣ በማህበራዊና ስነልቦናዊ ድጋፍ እንዲሁም በህጻናት ጉዳይ አያያዝ ላይ ያተኮረ መሆኑን አስረድተዋል:: ስልጠናው ከዚህ ቀደም የኢትዮጵያ መንግስት ከዓለም ባንክ ባገኘው ድጋፍ በትግራይ፤ በአፋር፤ በኦሮሚያ በቤኒሻንጉል ጉምዝ ክልል በግጭት ምክንያት የተጎዱ ማህበረሰቦችን መልሶ ለማቋቋም የነደፈው የአምስት ዓመት ፕሮጀክት የትግበራ እንቅስቃሴ አካልም ነው::

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርና የጤና ሚኒስቴር ከዓለም ባንክ ጋር በመተባበር ያዘጋጁት ይሄው ስልጠና በጦርነት ተጎጂ ለሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች የተቀናጀ ተግባራዊ ምላሽ ለመስጠት እንዲቻል መሆኑን የገለጹት ሚኒስትር ዴኤታዋ፣ ስልጠናው ጾታዊ ጥቃትን መከላከልና ምላሽ እንዲያገኝ ማድረግንም ታሳቢ እንዳደረገ ተናግረዋል:: ስልጠናው የተሰጠው ለሐይማኖት አባቶችና ለታዋቂ ግለሰቦች ሲሆን የማህበራዊና የአእምሮ ጤና ባለሞያዎችም በስፋት ተሳትፈውበታል::

በስልጠናው ተካፋይ ከሆኑ ግለሰቦች አንዱ ብያና ዋኬኖ፣ የመጡት ከምዕራብ ወለጋ ነጆ ወረዳ ነው:: የወረዳው ማህበረሰብ አስተባባሪም ናቸው:: ወረዳው ከፍተኛ ተፈናቃይ ያለበት ሲሆን፣ 15ሺ667 ተፈናቃይ አባ ወራ መኖሩን ይናገራሉ:: ከነዚህም የሴቶች ቁጥር 5 ሺ 569 ሲሆን የህፃናትና ታዳጊዎችም ቁጥር ከፍተኛ መሆኑን ያስረዳሉ:: ‹‹ለመፈናቀል የዳረገን ግጭት መነሻ ከቤኒሻንጉል ጉምዝ ጋር የሚያዋስን ድንበር ነበር›› በማለት የሚያስታውሱት ብያና ይሄው ችግር ስር እየሰደደ መጥቶ ወደ ከፍተኛ ደረጃ በመድረስ በርካቶችን ከቀያቸው ሊያፈናቅላቸው እንደበቃ ይገልፃሉ:: በዚህ መካከል በርካታ ሴቶችና ህፃናትም ለተለያየ ጥቃት መዳረጋቸውን ያወሳሉ:: በማንኛውም ችግር ወቅት ከሌላው ሕብረተሰብ በተለየ ሁኔታ ሴቶችና ህፃናት ለኢኮኖሚያዊ፤ ማህበራዊና ስነልቦናዊ ችግሮች መጋለጣቸውንና ለእነሱም ፈጥኖ መድረስ አስፈላጊ መሆኑንም ተናግረዋል:: 17 ወረዳ ባለው በምዕራብ ወለጋ ዞን ከ500 ሺህ ሕዝብ በላይ ከቀየው መፈናቀሉን የሚጠቁሙ መረጃዎች እንዳሉ የጠቀሱት እኚህ አባት፣ ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት ሴቶችና ህፃናት መሆናቸውን መገመት እንደሚቻልም ይናገራሉ::

ከቄለም ወለጋ ደንቢዶሎ የመጡት የስልጠናው ተሳታፊ አቶ ደሳለኝ ታፈሰ፣ በአካባቢው በተፈጠረ ችግር ነዋሪው መፈናቀል ብቻ ሳይሆን የተለያየ ችግር እንደ ደረሰበት አስረድተዋል:: በዚህም ህፃናት እናትና አባታቸውን አጥተዋል፣ ቤተሰብ ተለያይቷል፣ ቁጥራቸው ቀላል የማይባል ሰዎችም በግጭቱ ሞተዋል:: ከዚህ ውስጥ የቤተሰብ ኃላፊ በመሆናቸውና በተለያየ ምክንያት መሸሽ የማይችሉት ሴት ተጎጂዎች ቁጥር ከፍተኛ ነው:: ስልጠናው የሞቱትን ባይመልስም በሕይወት ያሉትን ችግር ይፈታል ብለው ያምናሉ:: ጉዳቱን በፀጋ ተቀብለው ለዳግም ሕይወት የመነሳሳት አቅም ከመፍጠር ጀምሮ ራሳቸውን እንዲያቋቁሙ ይረዳቸዋል የሚል ሀሳብም አላቸው:: ችግሩን ለመቅረፍ በተለይ ከአልባሳት ጀምሮ የተለያዩ ቁሳቁስና የምግብ አቅርቦት ድጋፍ በማድረግ እገዛ እየተደረገ እንደሚገኝም አቶ ደሳለኝ አስረድተዋል::

በምዕራብ ሸዋ ሴቶችና ህፃናት ቢሮ የሴቶች ንቅናቄ የሥራ ሂደት መሪ የሆኑት አሰልጣኝ እስካለች ቀነአ እንደሚሉት፣ ስልጠናው የተዘጋጀው በነሱ አካባቢና በተለያዩ አካባቢዎች በነበረው የሰላም ችግር ምክንያት የተፈናቀሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ችግሩን ተቋቁመው በትንሽ ድጋፍ ችግሩን ማለፍ እንዲችሉ ለማድረግ ነው:: ‹‹ሴቶች በሰላሙ እጦት ተደፍረዋል፤ ቤት ንብረታቸውን ተቀምተዋል:: ከኢኮኖሚና ከአካል በላይ በእእምሮና ስነልቦናቸው ላይ ከፍተኛ ችግር ደርሶባቸዋል›› ያሉት አሰልጣኝ እስካለች፣ እሳቸው የሚሰጡት ስልጠናም ይሄን ችግር መቅረፍና ሴቶች ከችግሩ እንዲያገግሙ ማስቻልን ያካትታል:: ከሚሰጧቸው ስልጠናዎች ዓይነትም የአእምሮ ጤና እና የስነ አእምሮና ማህበራዊ ድጋፍ (Mental Health and Pscho social Support)፣ የሴቶችና ህፃናት ጥቃትን እንዴት አድርጎ መምራት፣ ማስተናገድና ወደነበሩት እንዲመለሱ የሚያደርጉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ያተኮረ ነው::

አሰልጣኝዋ ስልጠናውን ከመስጠታቸው ቀደም ብሎ ሰልጣኞቹ በጉዳዮቹ ላይ ቀደም ብለው ምን ያህል ዕውቀት እንዳላቸው በዚያው የስልጠና ሂደት የሚገመገምበት ሁኔታ እንደነበረም አሰልጣኟ ተናግረዋል:: ሰልጣኞች ከስልጠናው ለውጥ ማምጣት የሚያስችል ግንዛቤ መጨበጣቸውን የሚያረጋግጥ ፈተና እንደወሰዱም አክለዋል::

‹‹በአብዛኛው በአእምሮ ጤና ላይ ስለምንሰራ ያገኙት ልምድና ዕውቀት ምን ያህል ያግዛቸዋል ብለን እንገመግማለን›› ያሉት አሰልጣኟ፣ ስልጠናው ሴቶችን ጨምሮ ሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ወደ ጤናቸው እንዲመለሱ ያስችላል ብለው ያምናሉ:: በተፈጠሩ የፀጥታ ችግሮች ተጎጂ የሆኑ ሰዎች አብዛኞቹ ተስፋ ስለቆረጡና በደረሰባቸው ችግር አእምሯቸው ስለተጎዳ ምንም መነሳሳት እንደሌላቸው የጠቆሙት አሰልጣኟ፣ ስልጠናው አእምሯቸውን ለሥራም ሆነ ለማንኛውም ዝግጁ እንዲሆኑ ያስችላል ተብሎ እንደታመነበት ያስረዳሉ::

ስልጠናው በተመሳሳይ በሌሎች አካባቢዎች ተሰጥቶም ሴቶች ወደ አምራችነትና ወደ ቀድሞ ሕይወታቸው እንዲመለሱ በማድረግ የተሻለ ውጤት ማምጣቱ ታይቷል:: በኦሮሚያ ክልል ባሉ ተጎጂ ሴቶች ላይም ከስልጠናው በኋላ ይሄው ሁኔታ ይመጣል ተብሎ እንደሚታሰብ ተናግረዋል::

ሲስተር ካሰች ለታ ከአርሲ ዩኒቨርሲቲ ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የመጣች ሲሆን ስልጠናውን ከሰጡ ባለሙያዎችም አንዷ ናት:: ሲስተር ካሰች ስልጠናውን የሰጠችው በአእምሮ ጤና ላይ ሲሆን ስልጠናው በሴቶችና ህፃናት ላይ በሰላም እጦት ከደረሰው ችግር አንፃር አስፈላጊና ወሳኝ መሆኑን ታስረዳለች:: እንደ ምክንያት የምታነሳውም ሴቶች፤ ህፃናትና፤ አቅመ ደካማ የሕብረተሰብ ክፍሎች ለአደጋው ሲጋለጡ በርካታ ችግሮች የሚደርሱባቸው መሆኑን ነው:: ከሚደርስባቸው ችግር አንዱና ዋንኛው የስነ ልቦና ችግር መሆኑንም ታወሳለች:: የአእምሮና አካላዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር የሚደርስባቸው መሆኑንም ታክላለች::ከዚህ ችግር ውስጥ ወጥተው ወደ ቀድሞው ማንነታቸውና ሕይወታቸው እንዲመለሱ ለማስቻል ስልጠና መስጠት ወሳኝ መሆኑንም ትጠቁማለች::

‹‹ተጎጂዎቹ አካላቸውም ሆነ አእምሯቸው ጤናማ ካልሆነ ምርታማ መሆን አይችሉም:: ምርታማ ካለመሆናቸው ጋር ተያይዞም ድህነት ይመጣባቸዋል›› ስትልም ለሚመለከታቸው አካላት በየደረጃው ስልጠናውን መስጠት በሕብረተሰብ ክፍሎቹ ላይ በተለይም በሴቶች ላይ የሚደርሰውን ችግር እንደሚቀርፍ ታምኖበትና ከተሞክሮም ታይቶ ስልጠናው እንደተሰጠ ትናገራለች:: የስልጠናው ዓላማ ተጎጂዎቹ ሴቶች በአጠቃላይም የሕብረተሰብ ክፍሎች በጉዳቱ ምክንያት የደረሰባቸውን ጠባሳ አስወግዶ ትክክለኛ አቋም ያላቸው ምርታማ ዜጎች እንዲሆኑ ማስቻል መሆኑን ተናግራለች::

‹‹በግጭት ወይም በጦርነትና ይሄን ተከትሎ ከሚመጣ መፈናቀል ጋር የተደፈሩ፤ የተደበደቡና አካላቸው የጎደለ ሴቶች ይኖራሉ:: እነዚህ ጉዳቶች ደግሞ የአእምሮ በሽታ ያመጣሉ›› የምትለው ሲስተር ካሰች፣ ሰልጣኞቹ በስልጠናው ባገኙት ዕውቀት በመታገዝ የተጎጂዎቹን ችግር እየለዩ ለመፍታት መሰል ስልጠናዎች ያስፈልጓቸዋል ብላ ታምናለች:: ስልጠናው ሰልጣኞቹ የሚችሉትን የሴቶቹን አእምሮ ህመም ለይተው እንዲያክሙ የማይችሉትን ደግሞ በጊዜ ወደ ሌላ ሕክምና ተቋም እንዲልኩ ማድረግ የሚያስችል እንደሆነም አክላለች::

እንደ ሲስተር ካሰች ገለፃ፣ በስልጠናው የስነ ልቦና ባለሙያዎችን መካፈላቸው በፊናቸው የስነ ልቦና ምክር እየሰጡ ተጎጂዎቹ ካለባቸው ችግር ወጥተው ጤናማ ሕይወት እንዲኖራቸውና እንዲመሩም ያግዛል በዚህም ችግሮች ፈጥነው ይቀረፋሉ የሚል ተስፋ አላት:: ስልጠናውን ‹ወቅታዊ፤ አስፈላጊና አንገብጋቢ› ስትል ገልፃዋለች:: በተለያየ ጤና ድርጅት የአእምሮ ጤና ባለሙያዎች በብዛት ላይኖሩ እንደሚችሉ የምትጠቁመው ሲስተር ካሰች፣ ስልጠናውን የወሰዱ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በስልጠናው በመታገዝ ጉዳት የደረሰባቸውን ሴቶች እንዲያግዙ የሚያስችል መሆኑንም ትናገራለች:: ለአብነትም የስነልቦና ባለሙያዎች ምክር ለሚያስፈልጋቸው ምክር በመለገስ፤ ሕክምና ለሚያስፈልጋቸው ነርሶችና ብዙ ባለሙያዎች ስላሉ ጉዳት የደረሰባቸውን ለይተው ሕክምና እንዲሰጡ ያደርጋል:: በዚህ የአእምሮ ህመም ምልክት የሚታይባቸውን ሴቶች መርዳት ያስችላል:: በተለያየ ምክንያት አእምሯቸው የተጎዳ ሴቶች የዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያቸው ቀድሞ እንደነበረው አይሆንም:: ስልጠናው ተጎጂ ሴቶችን እንዲሁም አጠቃላይ የሕብረተሰብ ክፍሎችን በማነሳሳትና በማነቃቃት የማቋቋም ሥራ መሥራት እንደሚያስችልም ታብራራለች:: የአቅም ማጎልበቻ ስልጠናው በዋነኛነት በአዕምሮ ጤና፣ በጾታዊ ጥቃት ምላሽ አሰጣጥ፣ በማህበራዊና ስነልቦናዊ ድጋፍ እንዲሁም በህጻናት ጉዳይ አያያዝ ላይ ማተኮሩንም ትጠቁማለች:: የስልጠናው የመጨረሻ ግብም ተጎጂዎቹን ከገቡበት ችግር በማውጣት ወደ አምራች፣ ጤናማ፤ ሠላማዊና ምርታማ ማድረግ እንደሆነም አስተያየቷን ሰጥታለች::

ሰው ሠራሽ ጦርነትም ሆነ የተፈጥሮ ችግርና ሌሎች ማህበራዊ ቀውሶች ከሌሎች የሕብረተሰብ ክፍሎች ይልቅ ሴቶችን የበለጠ ተጎጂ እንደሚያደርጉ የተለያዩ ጥናቶች ይጠቁማሉ:: ከሰኔ 2013 እስከ ታህሳስ 2014 ዓ.ም በአማራ ክልል የነበረ ጦርነትን አስመልክቶ በክልሉ የተደረገ ጥናት የሚያሳየውም ይሄንኑ የሴቶችን ይበልጥ ለችግር ተጋላጭነት ነው:: መደፈር፤ መገደል፤ የንብረት ውድመት፤ ዝርፊያ፤ መፈናቀልና በዚህ ወቅትም ለተለያዩ አደጋዎች መጋለጥ የበለጠ በሴቶች ላይ ደርሷል:: በጦርነት ከተጎዱ የሕብብረተሰብ ክፍሎች መካከል ሴቶች ቁጥራቸው በእጅጉ የላቀ ሲሆን በጥናቱ እንደተመለከተው ከ409 ሺ በላይ ሴቶች ተጎጂ ናቸው:: ከ263 ሺ በላይ ደግሞ ህፃናት እንደሆኑ በጥናቱ ተመልክቷል::

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

**በበዙ ትናንቶች ድልድይ እየተሸጋገረ ዘመናትን አልፎ ዛሬ ላይ ደርሷል። ትናንትናን በዛሬ እየቃኘ ዛሬ ደግሞ አዲስ ዘመን ድሮ እያለ ኋላውን በትዝታ ይቃኛል፡፡ አዲስ ዘመን ድሮ ምን ይመስል ነበር… ቆየት ካሉ የአዲስ ዘመን ትዝታዎች ቀንጨብጨብ እያደረግን እንቃኛቸዋለን፡፡ በወሊድ ላይ ሳሉ ሕይወታቸው ባለፈ አንዲት ሴት ምክንያት ሆስፒታሎች ተወዛገቡ…ይለናል፤ በሻላ ሐይቅ ማዕድናት ተገኙ እንዲሁም ደግሞ በመዲናችን አዲስ አበባ በአንድ የአፍሪካ መሪ ላይ የግድያ ሙከራ ተደርጎ ነበር..ስመሆኑ ይህ መሪ ማነው..በዚሁ የግድያ ሙከራ ላይ በተሳተፉ ሦስት ወንጀለኞች ላይ ደግሞ የሞት ፍርድ ስስመፈረዱ የወጡ ዜናዎችን እንዲሁም የማህበረሰቡ የውስጥ ችግር ፈቺ የሆኑ ጥያቄዎች ከሚቀርቡበት መፍትሄ ቢሆንም(?) ገጽ ላይ አንዲት ሀሳብ በማካተት አቅርበንላችኋል።**

### በወሊድ ላይ ሕይወታቸው ባለፈው ሴት ምክንያት ሆስፒታሎች ተወዛገቡ

ባለፈው ከየካቲት ወደ ጥቁር አንበሳ የተላኩ ወይዘሮ ገኔ ሽኩር የተባሉ ነፍሰ ጡር ሴት ሕይወታቸው የማለፉ ምክንያት ሕክምና ሳይደረግላቸው በመቅረቱ ነው ሲሉ ቤተሰቦቻቸው ቅሬታቸውን ገለጹ፡፡ ሆስፒታሎቹ ግን የግለሰቧን አማሟት አንዱ በአንዱ በማሳበብ ተወዛገቡ፡፡ በአዲስ አበባ በወረዳ 4 የቀበሌ 59 ነዋሪና የሟቿ ባለቤት የሆኑት አቶ ሽምሱ ሙደሲር ባለቤታቸው ነሐሴ 28 ቀን 1989 ዓ.ም ሌሊት ድንገት ስለታመሙባቸው ወደ የካቲት 12 ሆስፒታል የወሰዷቸው መሆኑን ገልጠው፣ ነገር ግን የዕለቱ ተረኛ በወቅቱ የሕክምና እርዳታ ለማድረግ የማይችሉ መሆናቸውን ስለነገሩአቸው ወዲያውኑ ወደ ዘውዲቱ ሆስፒታል መውሰዳቸውን አመልክተዋል፡፡

**(አዲስ ዘመን መስከረም 10 ቀን 1989ዓ.ም)**

### በሦስቱ አሸባሪዎች ላይ የሞት ቀጣት ተበየነ

(ኢ.ዜ.አ) የግብጹን ፕሬዚዳንት ሆስኒ ሙባረክን አዲስ አበባ ላይ ለመግደል የሞከሩና ሁለት ኢትዮጵያውያንን ገድለው ሦስቱን ያቆሰሉ አሸባሪዎች በሞት እንዲቀጡ ትናንት ያስቻለው የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወሰነ፡፡ የፍርድ ቤቱ ቃል አቀባይ እንዳስታወቀው ሰውፊት ሃሰን፣ አብዱል ቃኒ፣ አብዱል ከሪም አብዱልናዲና አልአረብ ሳዲቅ ሃፊዝ በተባሉ ግብጻውያን ላይ ቅጣቱ የተበየነው አቃቤ ሕግ ያቀረበባቸው ማስረጃ በዝግ ችሎት ላይ ሲመለከት በነበረው ፍርድ ቤት በመረጋገጡ ነው፡፡

አሸባሪዎቹ ለወንጀሉ አፈጻጸም የሚረዱ የጦር መሣሪያዎችንና ፈንጂዎችን በሱዳን አየር መንገድ አስጭነው በአዲስ አበባ የአየር መንገድ ጽሕፈት ቤት እንዳኖሩና ተጨማሪ የጦር መሣሪያዎችንም ከአገር እንደገዙ የሚያረጋግጡ ማስረጃዎችን አቃቤ ሕግ ለፍርድ ቤቱ ማቅረቡን የገለጠው ይሄው የፍርድ ቤቱ ቃል አቀባይ፣ የሥራ ክፍፍል በማድረግ መኪናና ቤቶች በመከራየት አቅደው መንቀሳቀሳቸውንም የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ለፍርድ ቤቱ መቅረቡን አስረድቷል።

**(አዲስ ዘመን መስከረም 11 ቀን 1989ዓ.ም)**

### በሻላ ሐይቅ ማዕድንና ኬሚካል አስ ተባለ

(ኢ.ዜ.አ) በስምጥ ሸለቆ በሚገኘው ሻላ ሐይቅ እስካሁን ጥቅም ላይ ያልዋለ ከ388 ሚሊዮን ቶን በላይ ሶዳ አሽ ማዕድንና የሶዲየም ክሎራይድ ኬሚካል እንዳለ መረጋገጡን የአብያታ ሶዳ አሽ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ገለጹ፡፡ ሥራ አስኪያጁ አቶ ታከለ ውቤ እንዳመለከቱት 1987ዓ.ም የውጭና የአገር ውስጥ ባለሙያዎች ሐይቁ ላይ ባካሄዱት ጥናት የሶዳ አሽ ማዕድን ክምችትና በአምስተኛ ደረጃ ደግሞ ሶዲየም ክሎራይድ ኬሚካል መኖሩ ተረጋግጧል፡፡

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 19 ቀን 1989ዓ.ም)**

### በአንድ የመናዊ ላይ ተደራራቢ ክሶች ተመሰረቱ

(ኢ.ዜ.አ) በሕግ ያልተፈቀደላቸውን የመንግሥት መሬት ተመርተዋል፣ በሕገ ወጥ ካርታ ከባንክ 10 ሚሊዮን ብር ተበድረዋል፣ ለኢትዮጵያውያን ብቻ በተፈቀደ የባንክ ሥራ ላይም ተሳትፈዋል በተባሉ አንድ የመናዊ ላይ አቃቤ ሕግ ክስ መሠረተ። ምክትል ረዳት ጠቅላይ አቃቤ ሕግ ሳህሉ ገብረየስ ትናንት ለኢዜአ እንዳስታወቁት፣ ግለሰቡ በተለያዩ ደረጃ ላይ ከነበሩ ባለሥልጣናት ጋር በጥቅም በመጎዳኘት ፋብሪካዎችን አቋቁማለሁ በሚል 463 ሺህ 380 ካሬ ሜትር በቡራዩ እንዲሁም 86ሺህ ካሬሜትር መሬት በቃሊቲ ከተሞች ያለ በቂ የፕሮጀክት ጥናት ወስደዋል። በዚህ ድርጊት ተሳትፈዋል የተባሉ ባለሥልጣናት ተከሰዋል። አቃቤ ሕጉ እንደሚሉት ግለሰቡ “ከቀበሌ ሹሞች ጋር በመመሳጠር ደስ ሲላቸው አህመድ አብዶ፣ ሌላ ጊዜ አህመድ ረመዳን ወይንም አህመድ አብዶ አልረመዳን ሲያሻቸው ደግሞ አህመድ አብዶ መሃመድ በማለት በአራት ስሞች በተለያዩ የእድሜ ዘመናት በተነሷቸው ፎቶግራፎችና መታወቂያዎች ይጠቀማሉ። በዜግነትም አንዴ የመናዊ ሌላ ጊዜ ደግሞ ኢትዮጵያዊ ነኝ ይላሉ”። በተመሠረተው ክስ መሠረት ግለሰቡ በተዘጋጁላቸው የተለያዩ ስሞችና መታወቂያዎች በቡራዩ አካባቢ አቶ አህመድ አብዱ አልረመዳን፣ በአቃቂ ደግሞ አህመድ አብዶ መሃመድ ተብለው ለሕዝብና ለመንግሥት ከፍተኛ ጥቅም ሊያስገኙ የሚችሉ ሰፋፊ የመንግሥት ቦታዎችን ከልለው በመያዝ ተደራራቢ ወንጀሎች ተከሰው ፍርድ ቤት ቀርበዋል።

**(አዲስ ዘመን መጋቢት 24 ቀን 1988ዓ.ም)**

### መፍትሄ ቢሆንም(?) የሚስቴን እህት ምከሩልኝ

ጥያቄ እኔ ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት ነኝ። ባለቤቴ በአሁኑ ወቅት ያለችው ውጭ አገር ነው። ከሕፃንነቷ ጀምሮ ያሳደኳት የባለቤቴ እህት ግን የምትኖረው እኔ ጋር ሲሆን የ14 አመትና የ8ኛ ክፍል ተማሪም ሆናለች። በጣም አስቸጋሪ እድሜ በመሆኗ ባለቤቴ በነበረች ጊዜም ሆነ ዛሬ ከመምከር አልተቆጠብኩም። እሷ ግን ባሰባት። ይልቁንስ ጎረምሶች ይዛ ወደቤት እየመጣች በኢኮኖሚ ትጎዳኛለች። ወደቤተሰቦቿ እንዳልካት አቅጣጫዋን ቀይራ ለጉዳት ትዳረጋለች ብዬ ሰጋሁ። እኔ ጋር እንዳትቆይም ላልተፈለገ እርግዝና፣ ለአባላዘር በሽታና ለኤድስ እንዳትዳረግ ፈራሁ። እና ምን ባደርግ ይሻለኛል?

**ዘለቀ ባንጆቱ ከአዲስ አበባ**

# ዓለም አቀፍ

## በካርቱም የሚደረገው ውጊያ ለሦስተኛ ቀን ተጠናክሮ ቀጥሏል



ካርቱምን ጨምሮ በበርካታ የሱዳን ከተሞች በአገሪቱ ጦር እና በፈጥኖ ደራሽ ልዩ የሚሊሻ አባላት መካከል የሚደረገው ውጊያ ለሦስተኛ ቀን ተጠናክሮ ቀጥሏል። በውጊያው ከ100 ያላነሱ ሰላማዊ ሰዎች መገደላቸውን እና ከ1ሺህ 100 በላይ ደግሞ መቁሰላቸውን የዶክተሮች ስብስብ የሆነ ኮሚቴ ተናግሯል።

የዓለም ጤና ድርጅት ደግሞ 83 ሰዎች መሞታቸውን አረጋግጫለሁ ብሏል። ከሟቾቹ መካከል ሦስቱ የተባበሩት መንግሥታት የዓለም ምግብ ፕሮግራም ሠራተኞች ናቸው። ግድያውን ተከትሎ የዓለም ምግብ ፕሮግራም በሱዳን ያለኝን ሥራ አቋርጫለሁ ብሏል።

ሁለቱም ተዋጊ ኃይሎች በካርቱም እንደ አየር ማረፊያ፣ ወታደራዊ ማዘዣ ጣቢያዎችን፣ ብሔራዊ ቴሌቪዥን ጣቢያ እና ቤተ-መንግሥትን ተቆጣጥረናል ሲሉ እርስ በእርሱ የሚጣረስ መረጃ ሲያወጡ ነበር። ተዋጊዎቹ ኃይሎች ትናንት እሁድ ረፋድ ላይ ለሰብዓዊነት ሲባል ለጥቂት ሰዓታት የዘለቀ የተኩስ አቁም ስምምነት አድርገው ነበር። በዚህ የተኩስ አቁም ጊዜ ውስጥ የቆሰሉ ወደ ሕክምና ተጓጉዘዋል።

ሀኪሞች በካርቱም ሆስፒታሎች ያለው ሁኔታ እጅግ ከባድ መሆኑን እና ውጊያው ባለሙያዎች እና የህክምና ግብዓቶች ወደ ጤና ተቋማት እንዳይደርሱ እክል መሆኑን እየተናገሩ ነው። በግጭቱ ውስጥ ሁለት ዋነኛ ተዋናዮች አሉ። ጀኔራል አብደል ፈታህ አል-ቡርሃን እና ጀኔራል መሐመድ ሐምዳን ዳጋሎ።

ላለፉት ሦስት ቀናት ውጊያ ገጥመው የሚገኙት በጀኔራል አብደል ፈታህ አል-ቡርሃን የሚመራው የአገሪቱ መደበኛ ጦር ሠራዊት እና በጀኔራል መሐመድ ሐምዳን ዳጋሎ የሚመራው የፈጥኖ ደራሽ ልዩ የሚሊሻ አባላት ናቸው። እነዚህ ሁለት ጀኔራሎች እአአ 2021 ላይ የሲቪል መንግሥቱ ከሥልጣን ከተወገደ በኋላ ሱዳንን ሉዓላዊ ምክር ቤት በሚል ሲመሩ ቆይተዋል።

የአገሪቱ ጦር አዛዥ ጀኔራል አብደል ፈታህ አል-ቡርሃን የሉዓላዊ ምክር ቤቱ ዋነኛ ሰው ሲሆኑ የፈጥኖ ደራሹ ልዩ ኃይል አዛዥ ጀኔራል መሐመድ ሐምዳን ዳጋሎ ደግሞ ምክትል ናቸው። እነዚህ ሁለት የጦር ጀኔራሎች በሱዳን ስልጣን ለሲቪል አስተዳደር ለማስተላለፍ ተስማምተናል ብለው ነበር። እንዲሁም የልዩ ኃይል አባላቱ ወደ አገሪቱ ጦር እንዲቀላቀሉ ተስማምተዋል።

ሄምቲ በሚለው ቅጽል ስማቸው የሚታወቁት ጀኔራል የሚመሩት 100ሺህ አባላት ያሉት ልዩ ኃይል፣ የአገሪቱን ጦሩን መቼ ይቀላቀላል፤ ጥምር ጦሩንስ ከዚያ በኋላ ማን ይመራዋል በሚለው ላይ ሁለቱ ጀኔራሎች መግባባት አልቻሉም።


ጀኔራል አል-ቡርሃን የሚሊሻ አባላቱ በሁለት ዓመት ውስጥ ወደ አገሪቱ ጦር መግባት አለባቸው ሲሉ ሄምቲ በሚለው ቅጽል ስማቸው የሚታወቁት ጀኔራል ሞሐመድ ሐምዳን ዳጋሎ ግን የሚመሩት ኃይል ጦሩን የሚቀላቀለው ከ10 ዓመት በኋላ ነው ይላሉ።

በዚህ ልዩነት ውጥረት ሰፍኖ ከቆየ በኋላ ግጭት በካርቱም እና በሌሎች ከተሞች ተቀስቅሷል። እሁድ እና ሰኞ ንጋት ላይ ልዩ የሚሊሻ ኃይል አባላቱ በካርቱም ቁልፍ ቦታዎችን መቆጣጠራቸው ተዘግቧል። ፕሬዚዳንታዊ ቤተ-መንግሥት፣ የኦማድሩማን ከተማ፣ የዳርፉር ግዛት እና በሰሜናዊ አገሪቱ የምትገኘው ሜሮዌ አየር ማረፊያን መያዛቸው ተዘግቧል።

የአገሪቱ ጦር በበኩሉ የልዩ ኃይል አባላቱ ቁልፍ ቦታዎችን አልያዙም ይላል። ሮይተርስ የዜና ወኪል የዓይን እማኞችን ጠቅሶ እንደዘገበው የአገሪቱ ጦር በጦር ጀቶች አማካይነት የልዩ ኃይል አባላቱ ጦር ሰፈሮችን በመደብደብ አንዳንድ ስፍራዎችን እየተቆጣጠረ ነው።

በጦርነት ቀጣና ውስጥ የሚገኙት የካርቱም ነዋሪዎች በፍርሃት እና ድንጋጤ ውስጥ ገብተዋል። «ለ24 ሰዓታት አልተኛንም» «በጣም ፈርተናል። ከፍተኛ የፍንዳታ ድምጽ ስላለ በዚያም የተነሳ ቤታችን እየተናወጠ ለ24 ሰዓታት አልተኛንም» ስትል ሁዳ የተባለች የካርቱም ነዋሪ ለሮይተርስ ተናግራለች። ድንገት የተቀስቀሰው ግጭት ከቤታቸው ርቀው ያሉ ሰዎችን መንቀሳቀስ እንዳይችሉ አድርጓቸዋል።

ሁዳ «የስኳር ሕመምተኛ አባት አለኝ። ምግብ፣ ውሃ እና መድኃኒት ያልቅብናል ብዬ እፈራለሁ» ብላለች። ካሎሆድ ካሃኢር የተባሉ ነዋሪ ደግሞ «ሁሉም ሰላማዊ ሰዎች ከቤት እንዳይወጡ ተነግሯቸዋል። ግን ይሄ የማንንም ደኅንነት ማረጋገጥ አይችልም» ማለታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።



# ስፖርት

## የቅርጫት ኳስ ብሄራዊ ቡድን ለማቋቋም የገጠመው የበጀት እጥረት

አስማየሁ ግዛው

ለክፍለ ዘመን የተጠጋ እድሜ እንዳለው ይነገራል፤ የቅርጫት ኳስ ስፖርት። ጅማሮውን በአሜሪካ ያደረገው ይህ ስፖርት በዚህ ወቅት በስፋት ከሚዘወተሩ ስፖርቶች ጎራ መሰለፍ ችሏል። ስፖርቱ ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍሎች መስፋፋቱን ተከትሎም ኢትዮጵያ ቀድመው ከተቀላቀሉ የአፍሪካ አገራት ቀዳሚ ነች። እአአ በ1949 ዓለም አቀፉን የቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን በአባልነት ከመቀላቀል ባለፈ፤ የአፍሪካ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን ቻምፒዮናን ከመሰረቱት አባል አገራትም ተጠቃሽ ናት።

ይህም በቅርጫት ኳስ ረጅም ታሪክና ልምድን ያካበተች አገር ያሰኛታል። ስፖርቱን በኢትዮጵያ ያስተዋወቁት ከካናዳ የመጡ የሰውነት ማጎልመሻ መምህራን መሆናቸው ይነገራል። ከዚያን ወዲህም በአዲስ አበባ በሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ሲስፋፋ፤ ቀስ በቀስም ዳብሮ በበርካታ የኢትዮጵያን ክፍሎች ሊዘወተር ችሏል።

የኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ብሄራዊ ቡድን በአንድ ወቅት ከአፍሪካ ምርጥ ቡድኖች አንዱ መሆን ቢችልም ከ1960ዎቹ ወዲህ ግን ተዳክሞ በዓለም አቀፍ ውድድሮችም መሳተፍ ቅንጦት ሆኖባታል።

የኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን ብሄራዊ ቡድኑን ወደ ቀደመ ዝናው ለመመለስ ጽኑ ፍላጎት ቢኖረውም ችግሮች እንደገጠሙት አስታውቋል። ፌዴሬሽኑ በበርካታ ዓለም አቀፍ ውድድሮች እንዲሳተፍ ግብዣ ቢደረግለትም በፋይናንስ እጥረት ምክንያት መሳተፍ አልቻለም። በዓለም አቀፍ ውድድሮች በሁለቱም ጾታዎች ከታዳጊዎች እስከ አዋቂዎች ውድድሮች ሲኖሩ እድሉን ለመጠቀም ከኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር የበጀት ድጋፍ እንዲደረግለት ቢጠይቅም ሊመለስለት አልቻለም። ይልቁንም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የዶላር እጥረት ስላለበት ድጋፍ ለማድረግ እቸገራለው የሚል መልስ እንደሰጠውም ፌዴሬሽኑ ጠቅሷል። ነገሩን አዳጋች ያደረገውም ለአንድ ውድድር ምዝገባ ብቻ ከ6ሺ ዶላር በላይ ማስፈለጉ ነው።



የቅርጫት ኳስ ስፖርት በብዙዎች ዘንድ ቢወደድም አገርን የሚወክል ብሔራዊ ቡድን ማቋቋም አልተቻለም፣

የኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ዳዊት አሳምነው፤ እንደ አገር የተዘጋጀና በየቀኑ ስልጠና የሚወስድ ባይሆንም ፌዴሬሽኑ ብሄራዊ ቡድን እንዲኖር እቅድ እንዳለው ያብራራሉ። ነገር ግን እቅዱን ለማስፈጸም ከፍተኛ የፋይናንስ እጥረት ገጥሞታል። እንደ አቶ ዳዊት አስተያየት ሁሉንም ስፖርት በእኩል የማየት ልምድ የለም። እንደ እግር ኳስና አትሌቲክስ የመሳሰሉ ስፖርቶች ዓለም አቀፍ ውድድሮች ሲኖሩ ድጋፍ እንደሚደረግላቸው ያነሱት ኃላፊው ለሌሎች ስፖርቶችም መሰል ድጋፎችን በማድረግ እኩል ማየት እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ሁሌም በምስራቅ አፍሪካ የዞን አምስት ቅርጫት ኳስ የሚካፈለው ብሄራዊ ቡድኑ ዘንድሮም ተሳታፊ ለመሆን መንግስት የፋይናንስ እገዛን ማድረግ እንደሚገባውም ኃላፊው አንስተዋል። ምክንያቱም ከመሰል ችግሮች በቀር በወንድም ሆነ በሴት በታዳጊ እንዲሁም በአዋቂ ለብሄራዊ ቡድን የሚበቁ ተጫዋቾች አሉ። በሌላ በኩል በመንግስት የሚመደበው ዓመታዊ በጀት እስከ አሁን አልተለቀቀም፤ በመሆኑም ፌዴሬሽኑ እየተንቀሳቀሰ የሚገኘው ከክለቦች ምዝገባና ከስፖንሰር በሚያገኘው ገንዘብ ነው። የአገር ውስጥ ውድድሮችንም እየመራ የሚገኘው ከደጋፊ አካላት በሚያገኘው ገንዘብ ነው። በቀጣይም ፌዴሬሽኑ ብሄራዊ ቡድኑን ለረጅም ጊዜ ስፖንሰር የሚያደርጉትን ተቋማት ለማግኘት እቅድ ይዞ እየሰራ ይገኛል።

ፌዴሬሽኑ ካስቀመጣቸው ዕቅዶች መካከል ስልጠናና ውድድር ላይ ከፍተኛ ትኩረት ማድረግ አንዱ ነው። የኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፕሪምየር ሊግም ሁለተኛ ዙር ተጠናቆ ሶስተኛ ዙር ውድድሩን ለመጀመር ዝግጅት እያደረገ ነው። የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ከተከሰተ ወዲህ በሜዳና ከሜዳ ውጪ የሚደረጉ ውድድሮች ቀርተው የዙር ውድድሮችን መደረግ መጀመሩን አቶ ዳዊት ይጠቁማሉ።

ክለቦቹ ተቀራራቢ ነጥብ ስላላቸው ውድድሮች በገለልተኛ ሜዳዎች እንዲካሄዱ ተደርጓል። ቀሪ ሶስት ጨዋታዎችም በተመሳሳይ በገለልተኛ ሜዳ የሚደረጉም ይሆናል። ገለልተኛ ሜዳዎቹ ሲመረጡም የቅርጫት ኳስ ከፍተኛ አቅም ያለባቸውን ስፍራዎች ማዕከል በማድረግ ነው።

በመስከ ምልከታ በተገኘ ግብዓትም የጋምቤላ ዩኒቨርሲቲ በውድድሩ እንዲሳተፍ መደረጉንም ፌዴሬሽኑ ጠቅሷል። በመሆኑም አራተኛውን ዙር በጋምቤላ ለማድረግ በእቅድ ደረጃ ተይዟል። እንደ ጋምቤላ፣ ደቡብ እና ምስራቅ ኢትዮጵያ የስፖርቱ አቅም ባለባቸው ስፍራዎችም ውድድሮችን ተዟዙሮ በማድረግ ጥሩ ስፖርተኞችን ለማግኘት እንደሚሰራም ኃላፊው ጠቁመዋል።

በኢትዮጵያ ቅርጫት ኳስ ፕሪምየር ሊግ በወንዶች አምስት ክለቦች ተሳታፊ ሲሆኑ፤ በሴቶች ደግሞ አራት ክለቦች ተካፋይ ናቸው። ክለቦቹ በአንድ ዙር በአጠቃላይ 16 ጨዋታዎችን የሚያደርጉም ይሆናል።


**ኦሮሚያ ክልል**

የባለንብረቱ ስም መሀመድ አለማየሁ ሰሌዳ ቁጥር ኦሮ 49553 ኦሮ ሊብሬ ቁጥር 0252240 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ባለቤትነት ታርጋ ጠፋብኝ ብለው በቀን 21/7/2015 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የባለቤትነት መታወቂያ ታርጋ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ታርጋ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በኦሮሚያ ትራንስፖርት ኤጀንሲ የጅማ ዞን ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

**ሲዳማ ክልል**

የባለንብረቱ ስም አቶ ፀጋዬ አጋፋር ተሽከርካሪው አይነት ሞተር ሰሌዳ ቁጥር 02 ደህ A09921 የፊት /የኃላ ሰሌዳ ጠፋብን ብለው በቀን 06/06/2015ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ ስለዚህ ሰሌዳው ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ለጽ/ቤቱ ሪፖርት እንዲያደርጉ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑ እንገልፃለን፡፡

**ሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የሀዋሳ ከተማ አስተዳደር ትራንስፖርትና መንገድ ልማት መምሪያ**

**የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ**

በአዲስ አበባ ከተማ ቦሌ ክ/ከ ወረዳ 08 የቤት ቁጥር 393ቤ.ቁ.87 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0058010309 ሚሼል ደስታ ኃይሌ በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት በገቢዎች ሚ/ር ቦሌ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት የእጅ በእጅ ሽያጭ ተጨማሪ እሴት ታክስ /ቫት/ ደረሰኝ ውስጥ ቁጥር 0018 ያልተሰራበት /አንድ ቅጠል/ ስለጠፋብኝ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ በመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀስው በግብር/ታክስ ከፋይነት ለተመዘገብኩበት ቦሌ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያ ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**የግብር ከፋይ ስም ሚሼል ደስታ ኃይሌ**

**ኦሮሚያ ክልል**

የባለንብረት ስም የማነ ግርማይ ብስራት የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A34749 የተሽከርካሪዉ አይነት ድርብ አገልግሎት የሻሲ ቁጥር AHTFR29G707047693 ሞዴል KUN25L-PRMSHW የሞተር ቁጥር 2KDA877105 የሊብሬ ቁጥር 445650 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 29/7/2015 አመልክተዋል ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የቃሊቲ ቅ/ጽ/ቤት**

የባለንብረት ስም ኦርኪድ ቢዝነስ ግሩፕ ኃላ/የተ/የግ/ማ የሰሌዳ ቁጥር ኢት 03-01-39314 የተሽከርካሪዉ አይነት ደረቅ ጭነት ከ10 ኩንታል የበለጠ የሻሲ ቁጥር WJME3TRS30C215976 የሞተር ቁጥር 128516 የሊብሬ ቁጥር 0102410 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ ብለው 27/7/2015 አመልክተዋል፡፡ ሠሌዳው ወድቆ፣ ተሠርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ፣ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሠሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልፃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለስልጣን የንፋስ ስልክ ቅ/ጽ/ቤት**

**የደረሰኝ መጥፋት ማስታወቂያ**

በአዲስ አበባ ከተማ ጉለሌ ክ/ከ ወረዳ 01 የቤት ቁጥር 054 ግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) 0001988809 ማዕሩፍ እንድሪስ ማዕሩፍ ከተመዘገብኩበት ጉለሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት የህትመት ፍቃድ በማግኘት ካሳተምኩት ደረሰኝ ውስጥ የተጨማሪ እሴት ታክስ (ቫት) የእጅ በእጅ ሽያጭ ቁጥር 51 የተሰራበት ቢጫ 1 ቅጠል እና ከቁጥር 99 እስከ 100 የተሰራበት 2 ቢጫ ቅጠል 2 ሮዝ ቅጠል የጠፋ ስለሆነ በማንኛውም አካል እጅ ውስጥ ገብቶ ወንጀል እንዳይሰራባቸው እና የጠፋ መሆኑን የ3ኛ ወገን እንዲያውቀው ይህ ማስታወቂያ እንዲተላለፍ ተደርጓል፡፡ ነገር ግን ከደረሰኙ ውስጥ ተሰርቶበት ያገኘ ወይም ከድርጅቱ ግዥ በማከናወን ክፍያ ለመፈፀም በማስረጃነት የተቀበለ ማንኛውም ሰው ከላይ ለተጠቀሰው በግብር/ታክስ ከፋይነት ከተመዘገብኩበት ጉለሌ ክ/ከ አነስተኛ ግብር ከፋዮች ቅ/ፅ/ቤት ወይም በአቅራቢያው ለሚገኝ ገቢ ሰብሳቢ መ/ቤት በማሳወቅ በግብር/ታክስ አሰባሰብ ላይ ትብብር እንዲያደርግ አስታውቃለሁ፡፡

**ግብር ከፋይ ስም ማዕሩፍ እንድሪስ ማዕሩፍ**